

ምዕራፍ ሁለት

# የጸጋ ስጦታዎች

## የጸጋ ስጦታ የተገለጠባቸው ቃላት

በአዲስ ኪዳን የጸጋ ስጦታዎችን ለማመልከት የተጠቀሱት ቃላት ሥጦታዎቹ እንዲያው ከጸጋው የተነሳ የተሰጡና የመንፈስ ቅዱስ ስራ መሆናቸውን በመግለጥ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ለማድረግ የተሰጡ እንደሆኑ የሚገልጡ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በዓለም የምትገኘው የክርስቶስ አካል በመሆኗ ክርስቶስ በዚህች አካል አማካይነት ዛሬም የራሱን ፈቃድ፥ አገልግሎትና ቃል እያስተላለፈ የመሆኑ መግለጫ ናት። የአካሉ አባላት ወይም ብልቶች ሁሉ ማለትም ክርስቲያኖች ሁሉ በውስጣቸው በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስጦታ ወይም ስጦታዎች ተሰጥቷቸዋል። ስጦታዎቹ አገልግሎቶቹም ሆነ ውጤቶቹ የተለያዩ ናቸው። ዓላማቸው ግን አንድ ነው። ስጦታዎች የተሰጡት ለአካሉ መገንባትና መታነጽ እንጂ ለግለሰብ መታወቂያነትና ገናንነት አይደለም። አንዳንድ ስጦታዎች ደግሞ ከሌሎች ይልቅ ጎልተው ይታዩ እንጂ ከሌሎች የተሻሉ ወይም የበለጠ የሚጠቅሙ ናቸው ማለት አይደለም። ስጦታዎች ሁሉ አገልግሎት ላይ ሲውሉ በጌታ መሪነትና በፍቅር ተቆጣጣሪነት መሆን አለበት። ማናቸውም አገልጋይ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆነ መንፈሳዊ ብስለት ባላቸው ሰዎች ለመመርመር ክፍትና ዝግጁም መሆን ይኖርበታል። ስጦታ አገልግሎት ላይ በሚውልበት ጊዜ ደግሞ ከአግባብና ከስርዓት ውጪ መሆን አይገባውም።

የጸጋ ስጦታ ጎልቶ የታወቀበት የአዲስ ኪዳን ቃል "ካሪዝማ" የሚባለው ነው። 'ካሪዝማዊ ንቅናቄ ወይም እንቅስቃሴ' የሚለው ሐረግ ከዚህ ቃል የተወሰደ ሲሆን ንቅናቄው "የጸጋ ስጦታዎች በተለይም በ1ቆሮ.12 የተዘረዘሩቱ ተዘነጉ" ከሚል መነሻ የተቀሰቀሰ ንቅናቄ ነው። ይህ ንቅናቄ ቀደም ሲልም በፕሮቴስታንት ተሃድሶ ወቅትና ከዚያም በኋላ ካሉት ዓመታት ጀምሮ ቢታይም በዚህ ክፍለ-ዘመን መግቢያ የተከሰተው 'የአዲሱ ጴንጤቆስጣዊ' (neo-pentecostal) አዲስ እንቅስቃሴና ከክፍለ-ዘመኑ አጋማሽ ጀምሮ በጣም የተጋነነው ካሪዝማዊ ተሃድሶ ከጸጋ ስጦታዎች መካከል በጥቂቶቹ ላይ በማተኮር ሌሎችም እንዲሁም ሌሎችንም ተዛማጅ ትምህርቶች በማዘል ላይ ያተኮረ ነው።

በአዲስ ኪዳን በተለይም በ1ቆሮ.12 ከተጻፉት ስጦታዎች መካከል የከፊሉ በተግባር መገለጽና ያለመገለጽ ጉዳይ ካለፉት ጥቂት ክፍለ-ዘመናት ጀምሮ የታመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የሚጠያየቁበት ርዕስ ሆኗል። 'ጥቂቶቹ ስጦታዎች ተቋርጠዋል' የሚሉት ወገኖች ስጦታዎቹ ያበቁት ከሐዋርያት አገልግሎት በኋላ ወይም በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ወይም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ተጽፎ ባበቃበት ጊዜ ነው ይላሉ። ሌሎቹ 'ስጦታዎቹ ከቶ አልተቋረጡም' የሚሉት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የፈቀደውን ለማድረግ ባለስልጣን መሆኑን እና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማስረጃዎችን በማቅረብ እኒህ ስጦታዎች ያልነበሩት (የሌሉት) ቤተ ክርስቲያን ስላልፈለገቻቸውና እንዲገለጡ ስላልጸለየች እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲሰራባት ልቧን ስላልሰጠች ነው ይላሉ። ሥጦታዎች በዚህ ዘመን ይኑሩ ወይም የተወሰኑት ይቅሩ ወደፊት በምናነባቸው ገጾች ውስጥ እናያለን።

በአዲስ ኪዳን 'ስጦታ' የሚለው ቃል በተለያዩ መግለጫ ቃላት ተገልጦ እናገኘዋለን። አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት በጽርዕ ቋንቋ ዶማ (δομα)፥ ዶሲስ (δοσιs)፥ ዶሪያ (δορεα)፥ ዶሬማ (δορημα)፥ ዶሮን (δωρον)፥ ሜሪስሞስ (μερισμοs)፥ ካሪስ (χαρis) እና ካሪስ ከሚለው ስርወ ቃል የወጣው ካሪዝማ (χαρισμα) የሚሉት ቃላት ስጦታ የሚለውን አሳብ ማስተላለፊያ ተደርገው ተወስደዋል። ለነዚህ ከላይ ለተጠቀሱት ሰባት ቃላት ቢያንስ አንድ አንድ ጥቅስ መስጠት አስፈላጊ ስለሚሆን እንደ ቅደም ተከተላቸው ጥቅሶቹን እንይ። ካሪዝማ የሚባለውን ሰባተኛውን ግን በዚህ ክፍል መጨረሻ ላይ ሰፋ አድርገን የምንመለስበት ይሆናል። በአንዳንዶቹ በአማርኛው ሌላ መሳይ ቃላት ተተክተውበታል።

- ዶማ - ማቴ.7:11፤ ኤፌ.4:8

- ዶሲስ - ያዕ.1:17

- ዶሪያ - ዮሐ.4:10፤ 2ቆሮ.9:15

- ዶሬማ - ሮሜ.5:16፤ ያዕ.1:17 ('በረከት')

- ዶሮን - ማቴ.23:19 ('መባ')፤ ራዕ.11:10

- ሜሪስሞስ - ዕብ.2:4 ('ማደል' - መስጠት)

ከላይ የተመለከትናቸው ስድስት ቃላት ጠቅለል ባለ መልኩ የእግዚአብሔርንም ይሁን የሰውን ስጦታ ለማመልከት መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀመባቸው ቃላት ናቸው። ቀጥሎ የምንመለከተው 'ካሪዝማ' የሚለው ቃል ደግሞ በተለይ የሚያመለክተው ከመለኮት የመነጩና በጸጋ የተሰጡ ስጦታዎችን ለመሆኑ ከጥቅሱ እንረዳለን። በተለይ በጸጋ የተሰጡ መሆናቸውን ቃሉ የተሰራበት 'ካሪስ' የሚለው ስርወ-ቃል ያስረዳናል። 'ካሪስ' ማለት 'ጸጋ' ማለት ሲሆን ጸጋ ደግሞ ፈልገን ወይም ተገብቶን ያገኘነው ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተቀበልነውና በዓይኖቹ ፊት ያገኘነው ሞገስ እንደማለት ነው።

ካሪዝማ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን 17 ጊዜያት ተጠቅሷል። እየተመለከትን ያለነው የጸጋ ስጦታን ትምህርት በመሆኑና ለቃሉም ሚዛናዊ ትርጉም ይኖረን ዘንድ ሁሉንም ማየቱ ተገቢ ነውና እያንዳንዱን ቃሉ የተጠቀሰበትን ጥቅስ መመልከቱ አስፈላጊ ነው። ይህን ቃል ጴጥሮስ አንዴ ብቻ ሲጠቅሰው የቀሩትን አስራ ስድስቱን ጳውሎስ ነው የተጠቀመባቸው። ካሪዝማ የሚለው ቃል የተሰመረበት ቃል ነው።

1. ሮሜ.1:11 "ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁ።"

ካሪዝማ ብዙ ጊዜ ለብቻው የሚጠቀስ ቃል ሲሆን እዚህ ግን 'መንፈሳዊ' ከሚለው ቅጽል ጋር አብሮ ተጠቅሷል።

2. ሮሜ.5:15 "ነገር ግን <u>ስጦታው</u> እንደ በደሉ መጠን እንደዚያ አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎች ሞተዋልና ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ (ዶሪያ) ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።"

በዚህ ጥቅስ ስጦታን ለመጥቀስ ጳውሎስ ሁለት የተለያዩ ቃላት እንደተጠቀመ ከምንባቡ መረዳት አያዳግትም።

3. ሮሜ.5:16 "አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው (ዶሬማ) አይደለም። ፍርድ ከአንድ ሰው ለኩነኔ መጥቶአልና ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ።"

አሁንም ጳውሎስ በአንድ ጥቅስ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ቃላትን መጠቀሙን እናስተውላለን።

4. ሮሜ.6:23 "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።"

በዚህ ክፍል ጸጋና ስጦታ ለየብቻቸው የተለያዩ ቃላት ሳይሆኑ 'የጸጋ ስጦታ' የሚለው ቃል እንዳለ ካሪዝማ ስለተባለ ነው የተሰመረበት።

5. ሮሜ.11:9 "እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና (ካሪዝማታ) በመጥራቱ አይጸጸትምና።"

እዚህም እንደ ላይኛው አሳብ ተመሳሳይ ሆኖ ቃሉ ግን ነጠላ ሳይሆን የብዙ ነው። በጸጋ ስጦታዎቹ የሚል አሳብ ያለው ነው።

6. ሮሜ.12:6 "እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ <u>ስጦታ</u> አለን..."

እዚህም የተጠቀሰው ካሪዝማታ የሚለው የብዙ ቃል ነው።

7. 1ቆሮ.1:7 "እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም።" ልክ እንደ ሮሜ.6:23 ጸጋና ስጦታ በአንድነት ነው እንደ አንድ ስጦታ የተወሰዱት።

8. 1ቆሮ.7:7 "ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ።"

9. 1ቆሮ.12:4 "የጸጋም ስጦታ (ካሪዝማቶን) ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው።"

ይህ ቃል ለየት ያለ ይመስላል እንጂ ግን አይደለም። ለየት ያለ ያስመሰለውም 'የ...ም' የሚለው ቅጥያ የቅርጽ ለውጥ ስለሰጠው ብቻ ነው።

10. 1ቆሮ.12:9 "ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ <u>ስጦታ</u> (ካሪዝማታ) ለአንዱም..."

ከዚህም ስጦታ ጋር የተቆራኘው ቃል የብዙ ነው ማለት "ስጦታዎች" ተሰኝቶ ነው የተገኘው።

11. 1ቆሮ.12:28 "እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም

ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም አገዛዝንም የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።"

እዚህ ቦታ የተጠቀሰው ልክ 12:9 ላይ በተጠቀሰው መልክ ነው።

12. 1ቆሮ.12:30 "ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን?" የብዙ ቃል።

13. "የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ ፈልጉ።" የብዙ ቃል።

14. 2ቆሮ.1:11 "እርሱም ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፥ ያድነንማል፥ እናንተ ደግሞ ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን በብዙ ሰዎች በኩል ስለ ተሰጠን ስለ ጸጋ ስጦታ ወደ ፊት ደግሞ እንዲያድን በእርሱ ተስፋ አድርገናል።"

15. 1ጢሞ.4:14 "በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ (ካሪዝማቶስ) ቸል አትበል።"

ይህም ቃል የቅርጽ እንጂ የትርጉም ልዩነት የለውም።

16. 2ጢሞ.1:6 "ስለዚህ ምክንያት እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሳሳ አሳስብሃለሁ።"

17. 1ጴጥ.4:10 "ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደመሆናችሁ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ።"

ከላይ በአስራ ሰባቱም ጥቅሶች እንዳየነው የጸጋ ስጦታ የሚለው ቃል ሰፋና ጠበብ ያሉ ትርጉሞችን እየያዘ አገልግሎት ላይ ውሏል። ሰፋ ያለው የዘላለም ሕይወታችንንም እስከመጠቅለል ይሰፋል። ለምሳሌ ሮሜ.6:23 ላይ ካሪዝማ ተብሎ የተጠቀሰው ቃል በጠቅላላው በክርስቶስ ሞት የተሰጠንን የዘላለም ሕይወት ወይም ስለ ደኅንነታችን የሚያወሳ ቃል ሲሆን በ1ቆሮ.12:9 ላይ ደግሞ እንደ አንድ የአገልግሎት ስጦታ ተደርጎ ተጠቅሷል። በ1ቆሮ.7:7 ላይ ለጌታ አገልግሎት ብሎ ሳያገቡ መኖርን ስጦታ ሲለው በሮሜ 5:16 ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠውን ትልቁን ስጦታ ማለትም ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን "ስጦታ" ብሎታል። እንግዲህ ከነዚህ ምሳሌዎች ብቻ እንደምንገነዘበው ካሪዝማ የሚለው ቃል ትርጉም ሰፋም ጠበብም ሊል ይችላል። የቃሉን ትርጉም እንዲህ ከተመለከትነው የስጦታን ትርጉምና በአዲስ

ኪዳን የስጦታዎችን ምንነት መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል።

## የጸጋ ስጦታዎች ምንነትና ዓላማ

ለብዙ ሰዎች የጸጋ ስጦታ ትርጓሜ ከሁለት ነገሮች ማለትም ከመንፈስ ፍሬና ከተፈጥሯዊ ችሎታዎች ጽንሰ ሐሳብ ጋር ይጋጭባቸዋል። የጸጋ ስጦታ፥ የተፈጥሮ ችሎታና የመንፈስ ፍሬ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የጸጋ ስጦታዎች (ወይም *χαρισματα*) ከተፈጥሮ ችሎታዎች የተለዩ ነገሮች ናቸው። አንዳንዶቹ በቅርጽና በአሰራር ተመሳሳይ ቢመስሉም እንኳ በመሠረቱ ግን የተለያዩ ናቸው። የተፈጥሮ ችሎታዎች የምንላቸው ከጠባይ፥ ከአስተዳደግ ከባቢ ጋር የሚጎዳኙና በነዚህ ነገሮችም የሚቀረጹ ናቸው። ወይም ከአካባቢ ሁናቴ በልጅነት ወይም ከወላጆች በውርስ ሊገኙ የሚችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የተፈጥሮ ችሎታ የምንላቸው ድምፃዊነትን፥ የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ተሰጥዖዎችን፥ የአካል ማዳበሪያና የሥነ-ውበት ዝንባሌዎችንና የመሳሰሉትን ሊሆን ይችላል።

የመንፈስ ፍሬ ደግሞ በአንድ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ መንፈስ ቅዱስ ራሱ የሚያፈራቸውና የክርስትና ውበት የሚገለጽባቸው የክርስቶስ ባህርያት ናቸው። የመንፈስ ፍሬ በሙሉ በሁሉም አማኞች ሕይወት ውስጥ መታየት ይገባቸዋል እንጂ እንደ ጸጋ ስጦታ አንዱ ለአንዱ ሌላው ደግሞ ለሌላው የሚሰጡ አይደሉም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማለት አንድን ነገር ለትንሽ ጊዜ ግፉም አድርጎ በቅልጥፍና ሰርቶ በላጭነትን የማግኘት ችሎታ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሹመቶችም ለምሳሌ ሽምግልና፥ ዲቁና፥ ክህነት ስጦታ ሊባሉ ወይም ከስጦታ ጋር ሊጋጩ አይገባም። በአንፃሩ የጸጋ ስጦታን ካየን ከዚህ ማለትም ከሹመቶች፥ ከተፈጥሮ ሥጦታዎችም ሆነ ከፍሬዎች የተለየ ነው። ምንጩም ሆነ ዓላማው ሌላ ነው።

> ካሪዝማ ወይም ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ስጦታ ምንጩ የእግዚአብሔር ጸጋ (ወይም ካሪስ) ነው። ስጦታው በአማኙ ድካም የተገኘ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የሚሰጠን እኛ በስራችን እነርሱን የማግኘት መብት ስላለን ሳይሆን ዓለም የእግዚአብሔር ኃይል ስለሚያስፈልጋት ነው። የጸጋ ስጦታ መመዘን ያለበትም ሁሌም በውጤቱ ነው ማለት ነው። ስጦታው፤

የትኛውንም ስጦታ ለአንድ አማኝ ሲሰጥ ያ ስጦታ በተግባር ላይ የሚውልበትን ጥበብ፥ ጉልበትና ድፍረትም አብሮ ይሰጣል። ይሁን እንጂ ይህ ደግሞ ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላትና በክርስትና ሕይወት ከመብሰል ጋርም ይያያዛል። ሌላው ነጥብ ደግሞ ማንኛውም ስጦታ ሲሰጥ አብሮት የታሰረ ኃላፊነት እንዳለም ማወቅ ነው። ለምሳሌ ሮሜ.12:8 "የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፥ የሚገዛ በትጋት ይግዛ" ሲል የተቆራኘ ኃላፊነት መኖሩን መናገሩ ነው። ኃላፊነት ካለ ተጠያቂነትና መልስ መስጠትም አብሮት መኖሩ ግልጽ ነው። እያንዳንዱ ምዕመን የተሰጠውን ስጦታ ወይም መክሊት ምን እንዳደረገበት በፍርድ ቀን መልስ ይሰጥበታል። (ማቴ.25:14-30)

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከተፈጥሮ ችሎታ የተለየ ነው። ይሁን እንጂ ተቀራራቢ ባህርያት አሏቸው። ለምሳሌ፤

| የተፈጥሮ ችሎታ | የጸጋ ስጦታ |
|---|---|
| - ስንወለድ የምናገኘው | - ዳግም ስንወለድ የሚሰጠን |
| - ከወላጆች ወይም ከአካባቢ የምወርሰው ቢሆንም ምንጩ እግዚአብሔር ነው | - ከጌታ በቀጥታ የሚሰጠን |
| - ዓላማው የሰዎች በጎነት ነው | - ቤተ ክርስቲያንን ማነጽ |
| - ይታወቃል፥ ያድጋል፥ በልምምድ ይበለጽጋል | - ይታወቃል፥ ያድጋል፥ በልምምድም ይበለጽጋል |
| - ለእግዚአብሔር ክብር መዋል ይገባዋል፤ ይሁን እንጂ ላይሆንም ይችላል | - ለእግዚአብሔር ክብርና ለአማኞች መታነጽ መዋል ይገባዋል ይሁን እንጂ በአሉታዊ መልኩ ሲገለገሉበትም ይስተዋላል |

ተቀራራቢ ባህርያት ቢታይባቸውም እንኳን የተፈጥሮ ችሎታ ወደ ጸጋ ስጦታ የሚያድግ ወይም የጸጋ ስጦታ ወደ ተፈጥሮ ችሎታ የሚወርድ ፈጽሞ አይደሉም። አንድ ጠበቃ የነበረ ሰው ጌታን ሲቀበል ሰባኪ የግድ ይሆናል ወይም የኮሌጅ አስተማሪ ደኅንነትን ሲያገኝ የማስተማር ስጦታ ይሰጠዋል ሸ። እንደ ጌታ ፈቃድ ሊሆን ይችል ይሆናል። ነገር ግን በዓለም እንዲህ የነበረ በቤተ ክርስቲያንም እንዲህ መሆን አለበት አይባልም፥ ሊሆንም አይገባም። የተፈጥሮ ችሎታ ከደኅንነት በኋላ የመንፈስ ቅዱስ መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ድምፃዊነት የተፈጥሮ ችሎታ መሆኑ እሙን ነው። ያ ድምፃዊ ሲለወጥ በችሎታው ስጦታውን ሊገልጥበት ይችላል። ስብከተ-ወንጌል ወይም ማስተማር ወይም መምከር ቢሆን ስጦታው ይህን በዜማ ሊያስተላልፈው ይችላል። በመሠረቱ ግን የጸጋ ስጦታ ከተፈጥሮ ችሎታ የተለየ ነው። ይህ አጠቃላዩ የጸጋ ስጦታና የተፈጥሮ ችሎታ ግንኙነት ገጽታ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ የፈለገውን ስጦታ በፈለገው ጊዜና በፈለገው ቦታ ባልተጠበቀም ሁኔታ ሊገልጥ ይችላል። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ የጸጋ ስጦታዎች ግብታዊ በሆነ መንገድም ሊከሰቱና ሊገለጡ ይችላሉ ማለት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር በአንድ ቦታ አንድ ተአምር ሊያደርግ ቢወድና ተአምራት የማድረግ ስጦታ ያለው ሰው በዚያ ባይኖር ያ ሰው ከሌላ ቦታ ሊመጣ አያስፈልገውም። የእግዚአብሔር ስራ በመጀመሪያ ደረጃ በራሱ በእግዚአብሔር ሀልውና እንጂ በሰው ሀልውና አይደገፍምና።

የጸጋ ስጦታና የመንፈስ ፍሬም አንድ እንዳይደሉ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በክርስቲያኑ ውስጥ የክርስቶስን ባህርይ የሚያንጸባርቅ ሲሆን የጸጋ ስጦታ ግን በአገልግሎት መስክ የሚታይና የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚያሳይ መሆኑን ባለፉት ገጾች ተመልክተናል። የመንፈስ ፍሬ በሁሉም የሚጠበቅና ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ስጦታ በሁሉም አንድ አይደለም። ፍሬ የሚሆኑት ሲሆን ስጦታ የሚያደርጉት ነው። ፍሬ በጌታ መንፈስ ኃይል ብቻ የሚያፈሩት ሲሆን ስጦታ ግን ሰዎችም ተለማምደው የሚሞክሩትና ሰይጣንም አስመስሎ ሊሰራው የሚችለው ነው። ፍሬ አንድ ሲሆን ስጦታ ግን ብዙ ነው። እንግዲህ ስጦታና ፍሬ አንድ ያለመሆናቸውን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ገጾች በግልጽ ማየት እንችላለን።

የጸጋ ስጦታን ባህርያት ስንመለከት አያይዘን ማየት ያለብን ነገር እኒህ ባህርያት የሰጪውን የእግዚአብሔርን ባህርያት የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ነው። የስጦታዎቹ ምንጭና ሰጪ፥ ደልዳይና በመጨረሻም በስጦታዎቹ የሚከብረውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። የሥላሴ ሶስቱም አካላት በሰጪነት ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ በሮሜ.12:3 እግዚአብሔር መሆኑ በኤፌ.4:7 ክርስቶስ መሆኑ፥ በ1ቆሮ.12:9 መንፈስ ቅዱስ መሆኑ ተጠቅሷል። በተለይ በኤፌ.4 እንደምናገኘው ስጦታዎች የክርስቶስ የማረጉና በክብር በአብ ቀኝ የመቀመጡ

ውጤትና ማረጋገጫ ተደርገው የተሰጡ እንደሆኑ እናያለን። የከበረ ጌታ በሰማያት እንዳለንና በኛም ስጦታ እርሱ መላቅ እንደሚገባው ማወቅ እንዴት ያለ የተወደደ እውነት ነው! ስጦታዎች የተሰጡት ሰዎች ራሳቸውን እንዲያጎሉበትና በክርስቶስና በክርስቲያን መሃል የሆነ ግርዶሽ እንዲፈጥሩ ከቶ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በአንድ ስጦታ ስትባረክና ስትታነጽ መክበር የሚገባው የስጦታው ባለቤት ብቻ ነው። ይህ ማለት አገልጋዩ መናቅና መንኳሰስ አለበት ማለት አይደለም። እንዲያውም በአንጻሩ የዚህ የከበረ ጌታ አገልጋይ መሆን እራሱ የክብሩ ተካፋይነት በመሆኑ ትልቅ መታደል ስለሆነ ለእግዚአብሔር ሰዎችና አገልጋዮች ሁሉ ከሚገባው ክብር መጉደል የለበትም። አንድ አማኝ ከስጦታዎቹ ባለቤት ይልቅ ከስጦታዎቹ ጋር በፍቅር መውደቅ የለበትም። የማያልፈውን በሚያልፈው መለወጥ ከኪሳራ ሁሉ የከፋ ኪሳራ ነው። አንድ ስጦታ በማኅበረ ምዕመናን መካከል ሲከሰት ወይም ሲገለጥ የእግዚአብሔር ኃይልና ባህርይ በእርግጥ መታየት አለበት። የመንፈስ ፍሬዎች የጌታን ባህርይ እንደሚያሳዩ ሁሉ ስጦታዎቹም የእርሱን ማንነትም ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። አንድ ሰው ከተፈወሰ ወይም የፈውስ ስጦታ በዚያ ሰው ላይ ከተገለጠ የጌታ ፈዋሽነት በግልጥ ይታያል። አንድ ሰው ከሰበከም የጌታ ቃሉን ገላጭነት በዚያ ይታያል። በሌሎቹም የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ የጌታ ማንነት እንዲሁ መታየት ወይም መገለጥ አለበት።

## አማኞች ሁሉ ስጦታ(ዎች) ተሰጧቸዋል

ስጦታዎች ለአማኞች ሁሉ ተሰጥተዋል። ስጦታ ያልተሰጠው አማኝ የለም። አዲስ ኪዳን ይህን አበክሮ ያስተምረናል።

- "ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ስጦታ ተሰጠን።" (ኤፌ.4:7)

- "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።" (1ቆሮ.12:7)

- "እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ።" (1ጴጥ.4:10)

አንዳንድ ክርስቲያኖች ጥቂቶች ብቻ ስጦታ የሚሰጣቸውና ብዙዎች ያንን እየተካፈሉ እንደሚኖሩ እየመሰላቸው ይህንንም አሳብ ተቀብለው እንደ

ስታዲየም ተመልካች ሆነው በቤተ ክርስቲያን ይኖራሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በአንጻሩ ሁሉ ስጦታ ያላቸው እየመሰላቸው የአስር ወይም የአስራ አራት ሰዎችን አገልግሎት ብቻቸውን ለመሸፈን ሲታገሉ ይታያል። በቤተ ክርስቲያን ማለትም በክርስቶስ አካል አካል ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ክርስቲያን ቢያንስ አንድ ስጦታ አለው። ከአንድ በላይ ስጦታዎች ሊኖሩት ይችላል። ይሁን እንጂ ሁሉም ሊኖሩት ግን አይችልም። ይህ ከሆነ ያ ሰው ብልት መሆኑ ቀርቶ እራሱን የቻለ አንድ ባለ አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያን ሆነ ማለት ነው። ሁሉም ደግሞ አንድ ዓይነት ስጦታ አይኖራቸውም ይህ ከሆነ ደግሞ ያ አካል በአንድ ብልት ብቻ የተሰራ አካል መሆኑ ነው። እዚህ ላይ ነው በ1ቆሮ.12 ላይ ጳውሎስ የተጠቀመበት የአካልና ብልቶች ምሳሌነት ውበቱ የሚታየው። "አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መስማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መስማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ..." (1ቆሮ. 12:7)

የሚንቀሳቀስና ስራ የሚሰራ ብልት ይበልጥ ጠንካራ እንደሚሆን ስጦታዎቻችንን ባገለገልንባቸው መጠን እናድጋለን ይበልጥም እንሞረዳለን። ውሃ ሞልቶበት ከተቀመጠ በርሚል ይልቅ በየጊዜው እየተቀዳበት የሚያገለግል ታኒካ ይሻላል። አንድ አማኝ ስጦታውን ለማወቅ መጣርና በሚገባውም ቦታ መሰማራት ይጠበቅበታል። ለአማኝ ስጦታውን ያለመጠቀም ማለት አካሉን መጉዳትና የሚያገኘውን በረከት እንዳያገኝ ማደህየት እንደማለት ነው። እያንዳንዱ አማኝ ስጦታ ያለው የመሆኑ እውነት ያ ሰው በጌታ ቤት ውስጥ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጣል! ራሱን በንቀት ማየት እንደሌለበት መረዳት ይገባዋል።

ስጦታዎች የሚሰጡት እግዚአብሔር እንደወደደ እንጂ እኛ እንደመረጥን አይደለም። 1ቆሮ.12:11 ይህን እውነት ነው የሚያስተምረን። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ባለ ስልጣን መሆኑን ለወደደውም የወደደውን እንደሚሰጥ ከዚህም መረዳት እንችላለን። ይህም ደግሞ እግዚአብሔር በአካሉ ማለትም በቤተ ክርስቲያን በኩል ሊያከናውን ያለውን ዘላለማዊ እቅዱን ለመፈጸም ትክክለኛ የሆነውን ነገር የሚያደርግ የመሆኑ ማስረጃም ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ባለማስተዋል ያልተሰጣቸውን ነገር ለማግኘት በመጾምና በመጸለይ በመለማመድም ጊዜያቸውን ያባክናሉ ወደ ስህተትም ይወድቃሉ።

ስጦታ ለአንድ አማኝ የሚሰጠው መቼ ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ እጅግ በጣም ግልጽ ሆኖ አልተጻፈም። የስጦታዎች ዝርዝር በተጻፈባቸው ቦታዎች በግልጽ የምናገኘው አማኞች ሁሉ ስጦታ እንደተሰጣቸው ነው። አማኝ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበለው ደህንነትን በሚቀበልበት ጊዜ እንደመሆኑ ስጦታንም

የሚቀበለው ያኔ ነው። ስጦታ የሚሰጠው ከደኅንነት በኋላ የተወሰነ ጊዜ ተቆይቶ ቢሆን ኖሮ ይህ አሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ይበልጥ ግልጽ በሆነ ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ስጦታዎችን የሚሰጠን ዳግም በምንወለድበት ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ስጦታዎችን የሚያድለው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከሆነ ከደኅንነት በፊት ስጦታ ያለመኖሩ ግልጽ ነው ማለት ነው። አማኝ ዳግም በሚወለድበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ማደሪያ ሆኗልና በዚያን ጊዜ ስጦታንም ታድሏል። ዳግም ሲድን የአካል ብልት ሆኗልና ብልት ሲሆን እንደ ብልትነቱ የአገልግሎት ድርሻውንም ወዲያው ነው የተካነው። በሐዋ.8 እና 19 ውስጥ የምናገኛቸው ሳምራውያንና የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እጅ የተጫነባቸው የጸጋ ስጦታ እንዲቀበሉ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ነበር። በ1ጢሞ.4:14 እና 2ጢሞ.1:6 ላይ ለጢሞቴዎስ እጅ መጫኑ ስጦታ ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ መሆኑን የሚናገር አሳብ ነው። ጢሞቴዎስ ከዕድሜው ወጣትነትና ከተሰጠው ኃላፊነት ክብደት ጋር ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ የተሰጠበትን ሁኔታ የሚናገር መሆኑን ከዐውደ ንባቡ እንረዳለን።

ስጦታዎች አስቀድሞ ባሉን ዓለማዊ ትምህርቶችና የዕውቀት ችሎታዎችም አንፃር ተመዝነው አይሰጡንም። እኛ ስለፈለግንና ስለጸለይንም አይሰጡንም። 1ቆሮ.12:31 "ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ" ይላል። ይህን ሲል ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ ስለተጻፈው ስለ ፍቅር መናገሩ አይደለም። ምክንያቱም ፍቅር የመንፈስ ፍሬ እንጂ የጸጋ ስጦታ አይደለምና። ይህ ‘ፈልጉ’ የሚለው ትዕዛዝ ለእያንዳንዱ ምዕመን የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይሆን በማኅበረ ምዕመናን ደረጃ ለጠቅላላዋ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መታነጽ የሚበጀውን ነገር እንዲፈልጉ የተነገራቸው ነው። የቆሮንቶስ ምዕመናን በማነጽ ረገድ የሚበልጠውን ስጦታ (ትንቢትን) ትተው ከዚህ የሚያንሰውን ስጦታ (ልሳንን) በማጉላታቸው ትርምስ ውስጥ መግባታቸውን እያረመ የጻፈላቸው መልእክት ነው። ይበልጣል ሲባልም በማነጽ ረገድ ሁለቱ ሲነፃፀሩ ነው። ስጦታዎች የተሰጡን ከጸጋው የተነሳ ብቻ ነው። ካሪዝማ የሚለው ቃል ራሱ የሚነግረን ይህን እውነት ነው። ከጸጋው የተነሳ ብቻ የተሰጠን ከሆነ ደግሞ ማንም ስለ ስጦታው ሊኩራና ሊመካ አይገባውም ሰጪውን ከማመስገንና ከማክበር በቀር።

## የጸጋ ስጦታዎች ዝርዝር በአዲስ ኪዳን

በአዲስ ኪዳን የጸጋ ስጦታዎች የተዘረዘሩባቸውን ቦታዎች ጥቂት

ናቸው። እነዚህም ሮሜ.12:3-8፤ 1ቆሮ.12:4-11፤ 1ቆሮ.12:27-28፤ 1ቆሮ.13:1-3፤ ኤፌ.4:11 እና 1ጴጥ.4:10-11 ናቸው። 1ቆሮ.7:7ንም እንደ አንድ ስጦታ አድርገው ዝርዝር ውስጥ የሚያስገቡት አሉ።

1ጴጥ.4 መናገርና ማገልገል ብሎ በሁለት ስለሚከፍላቸው ሁለት ሌሎቹን ስጦታዎች የሚያቅፉ ዋና ዋና ክፍሎች እንደሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ይናገራሉ። እውነትም ስጦታዎችን ሁሉ ስንመለከት ወይ የመናገር ወይም የማገልገል ማለትም የማድረግ ስጦታዎች ናቸው። ስለዚህ ይህ ክፍል የስጦታዎች ዝርዝር ነው ከማለት ይልቅ ዋና ዋና የስጦታ ክፍሎችን የሚያመለክት ጠቋሚ ነው ማለት ይቻላል።

<u>በሮሜ 12</u> የስጦታዎችን ዝርዝር እናገኛለን። እነዚህም ትንቢት፥ አገልግሎት፥ ማስተማር፥ መምከር፥ መለገስ፥ መግዛትና መስጠት በጠቅላላ ሰባት ናቸው።

<u>በ1ቆሮ.12</u> የመጀመሪያው ክፍል ስጦታዎች ተዘርዝረዋል። እነዚህም ጥበብን መናገር፥ እውቀትን መናገር፥ እምነት፥ ፈውስ፥ ተአምራት ማድረግ፥ ትንቢትን መናገር፥ መናፍስትን መለየት፥ በልሳኖች መናገርና በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም በጠቅላላ ዘጠኝ ናቸው።

<u>በ1ቆሮ.12</u> ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ አስተማሪዎች፥ ተአምራት ማድረግ፥ መፈወስ፥ እርዳታ፥ አገዛዝ እና ልዩ ልዩ ልሳኖች በጠቅላላ ስምንት ተዘርዝረዋል።

በኤፌ.4 ደግሞ ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌል ሰባኪዎች፥ እረኞችና አስተማሪዎች በጠቅላላ አምስት ተጠቅሰዋል። አንዳንድ አስተማሪዎች የመጨረሻዎቹን ሁለቱን በመደረብ እና እንደ አንድ በመቁጠር ስጦታዎቹን በጠቅላላ አራት ያደርጓቸዋል። የመጨረሻው እዚህ ቢደረብም እንኳ በሌላ ቦታ ለብቻ ስለተጠቀሰ ስጦታነቱ እዚህ ድርብ ቢመስልም ነጠላዊ ነው።

እነዚህ ዝርዝሮች ናሙናዊ እንደሆኑ ይመስላል እንጂ ስጦታዎቹ እነዚህና እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይቻልም። ዝርዝሮቹን ለየብቻ ከደመርናቸው ከሰላሳ ቢዘሉም ከስጦታዎቹ አንዳንዶቹ አንድ ቦታ ተጽፈው ሌላ ቦታ ስለተደገሙ ድምራቸው ያን ያህል አያህልም። ከተደጋገሙት አንዳንዶቹ በዋናው ቋንቋ በተለያዩ ቃላት ተጽፈዋል ይሁን እንጂ በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ናቸውና የተለያዩ ስጦታዎችም አይደሉም።

አንዳንድ አስተማሪዎች ስጦታዎችን እንደየዓይነታቸው በመደልደል ተቀራራቢ የሆኑትን በቡድን በማድረግ ይከፋፍሏቸዋል። ለምሳሌ 'የማስተር ላይፍ' የደቀ መዝሙር ስልጠና መጽሐፍ በአራት ቡድኖች በመከፋፈል አገልግሎት ማስተማር፥ አምልኮና ምስክርነት ሲል ስይሟቸዋል። በአገልግሎት ስር መርዳት መማር፥ መስጠትና መግዛት ይገኛሉ። በማስተማር ስር ደግሞ ጥበብ፥ ዕውቀት፥ ማስተማርና ማበረታታት አሉ። በአምልኮ ስር እምነት፥ ፈውስ፥ ተአምራት፥ መለየት፥ ልሳን እንዲሁም ትርጉም ተደልድለዋል። በምስክርነት ስር ደግሞ ትንቢት፥ የወንጌል ስብከትና መጋቢነት ይገኛሉ።[2] ሌሎች አስተማሪዎች ደግሞ በሌላ መንገድና በሌሎች ቡድኖች ስር ይቀለኩሏቸዋል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስጦታዎቹን ለየብቻ ስለምንመለከታቸው በቡድናች ውስጥ መሆናቸውን እንደዚህ ከመናገር በቀር አናተኩርበትም። አንዳንድ ስጦታዎች እንደ ኩታ ገጠም መሬት የሚገናኙበት ከፊሎች ደግሞ አንዱ ከሌላው የሚጋሯቸው ባህርያት ሊኖሩ ይችላሉ። ቢሆንም ዝርዝሮቹን በንጠላ መመልከቱ ምንነታቸውን ይበልጥ ለመረዳት ያስችለናልና እስቲ እያንዳንዳቸውን ለየብቻ እንያቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ እያንዳንዱ ስጦታ ጥልቅ በሆነ መንገድ ለመመርመር አመቺ አይደለም። ነገር ግን ጊዜ ወስዶ ማጥናት የሚቻልበት አጋጣሚ ሲገኝ ርግጥ ነው ቀጠሮ የማይያዝለት ጉዳይ ነው። ለዚህም በዚህ ርዕስ ላይ የተጻፉ በርካታ መጻህፍትን ማየትና ሌሎችም ይህን የሚያስተምሩ የቡድን ስልጠናዎችን ለምሳሌ ከላይ እንደተጠቀሰው ያለውን የ'ማስተር ላይፍ' የደቀ መዝሙርነት ስልጠና ኮርስ ወይም ሌላ መሰል ዝግጅት መሳተፍ ወይም መውሰዱ ይበልጥ ለመረዳት ጥሩ መድረክ ይሆናል።

## የጸጋ ስጦታዎች በቀረቤታ ዕይታ

ቀጥሎ ባሉት ገጾች የጸጋ ስጦታዎችን ዝርዝር የምንመለከተው አዲስ ኪዳን ውስጥ በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሠረት ነው። መጀመሪያ ከሮሜ ከዚያም ከቆሮንቶስ በመጨረሻም ከኤፌሶን መጽሐፎች እናያቸዋለን። በነዚህ የዝርዝር ክፍሎች የተጠቀሱት ስጦታዎች በጠቅላላ ብዛታቸው አስራ ስምንት ሲሆን በአንዱ ላይ የተጠቀሱት በሌላው ላይ ቢደገሙም በዚህ መጽሐፍ ተደጋግመው ስለማይታዩ ቅደም ተከተላቸው ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፤

1. ትንቢትን የመናገር ስጦታ

2. የማገልገል ወይም የዕርዳታ ስጦታ

3. የማስተማር ስጦታ

4. የመምከር ስጦታ

5. የመስጠት ስጦታ

6. የመግዛት ስጦታ

7. የመማር ስጦታ

8. ጥበብን የመናገር ስጦታ

9. ዕውቀትን የመናገር ስጦታ

10. የእምነት ስጦታ

11. የፈውስ ስጦታዎች

12. ተአምራትን የማድረግ ስጦታ

13. መናፍስትን የመለየት ስጦታ

14-15. በልሳናት የመናገርና የመተርጎም ስጦታ

16. የሐዋርያነት ስጦታ

17. የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ

18. የእረኝነት ስጦታ

## ትንቢት የመናገር ስጦታ

በአንዳንድ ቦታዎች መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ትንቢት እንደተናገሩ ይናገርና ምን እንዳሉ አይገልጥም፥ ስለዚህም የተነገረው ነገር ይዘቱ ስለማይታወቅ ምንነቱንም መናገር ያዳግታል። የሚታወቁ የተነገሩ ነገሮችና ትንቢት እንደሆኑም የታወቁ ንግግሮች ደግሞ በቃሉ ውስጥ በብዛት ተጽፈውልናል። ትንቢትን መናገር ቢያንስ በሦስት ወይም በአራት መንገዶች ሊተረጎም ይችላል። እነዚህም፤

1. እግዚአብሔርን የማክበርን ነገር መናገር

2. ወደፊት የሚሆነውን ነገር መናገር

3. ለአንድ ወቅትና ቦታ ወይም ሰው ወይም ጉባዔ የሚሆን መልእክትን በግልጽና በማያሻማ መንገድና ቋንቋ ማስተላለፍ። ይህ መልእክት እንደ እግዚአብሔር ቃል ማለትም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ስልጣን ያለው ሳይሆን ሰሚዎቹ መርምረው የቅዱስ ቃሉን ሚዛን ሲያሟላ የሚቀበሉት መልእክት ነው።

4. የእግዚአብሔርን የተገለጠ ፈቃድ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን መግለጥ።

እነዚህን አተረጓጎሞች በመጠኑም ቢሆን ማብራሪያ በማከል መመልከቱ ተገቢነት አለውና እንደሚከተለው እንያቸው።

1. እግዚአብሔርን የማክበርን ነገር መናገር፤ ይህ በግልጽ ልናብራራው የማንችለው እግዚአብሔርን የማክበር ንግግር ነው። አንዳንድ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት እንደተናገሩ እንጂ ምን እንደተናገሩ በግልጽ አናገኝም። ከጠቅላላ አሳቡና ከዐውዱ የምናገኘው ግን ያ ንግግር እግዚአብሔርን የማክበር ንግግር መሆኑን ነው። (ለምሳሌ ሐዋ.19:6፤ 1ሳሙ.10:1-13 ወዘተ.) በሉቃ.1 የምናገኘው ዘካርያስ የተናገረው ትንቢት ዮሐንስ ወደፊት የሚሆነውን ነገር በመግለጡ (1:76-79) ወደፊታዊ (prophetic) ልንለው እንችላለን፤ ነገር ግን ከነዚህ ጥቅሶች ቀደም ብሎ የተናገራቸው ነገሮች (1:68-75) እግዚአብሔርን የሚያወድሱና የሚያከብሩ አሳቦች ናቸው። ይህን እግዚአብሔርን የማክበር ንግግር የዚህኛው የትንቢት ትርጉም ምሳሌ አድርገን ልንወስደው እንችላለን።

2. ወደፊት የሚሆነውን ነገር መናገር፤ ትንቢት የሚለው ቃል ራሱ ከወደፊት ነገርና ጊዜ ጋር የተዛመደ ነው። በሰዋሰዋችንም የኃላፊ፥ የአሁንና

የትንቢት ጊዜ እንደምንለው ማለት ነው። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን መናገር፥ መተንበይ ወይም ትንቢት መናገር ሲባል ተናጋሪውም ነቢይ ይሰኛል። በብሉይ ኪዳን ዘመን በጊዜያቸውና በአዲስ ኪዳን እንዲሁም በዚህና ከዚህም ዘመን በኋላ ስለሚሆኑት ነገሮች የተናገሩ ነቢያት ነበሩ። በአዲስ ኪዳንም ስለራሳቸው ዘመን፥ ስላለንበትና ስለ ዘመን መጨረሻም ትንቢት የተናገሩ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች የተናገሩትን ነገር የተናገሩት እግዚአብሔር አመልክቷቸው እንጂ ከሌላ ምንጭ ቀድተው አልነበረም። ለምሳሌ፤

- ሙሴ እግዚአብሔር ግብፅን እንደሚቀጣ አስቀድሞ ተናገረ።
- ዮሴፍ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚጎበኛቸውና ከግብፅም እንደሚያወጣቸው ትንቢት ተናገረ።
- ኤልያስ ስለሦስቱ ዓመት ተኩል ድርቅ ተናገረ።
- ኢሳይያስ ስለ መሲህ መወለድ ተናገረ።
- ዳንኤል ስለ መጪዎቹ መንግስታት ተናገረ።
- ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን መልክ ተናገረ።
- አጋቦስ በዘመናቸው ስለመጣው ረሃብ ተናገረ።

ሌሎችም ብዙ ተናግረዋል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዲህ ያሉት ነቢያት ትክክለኛነታቸውና ከእግዚአብሔር የተላኩ የመሆናቸው ሁለት ዋና ዋና መስፈርት አሉ። እነዚህም አንደኛ የተናገሩት ነገር መፈጸምና ሁለተኛ የህይወታቸው ምስክርነት ናቸው። እኒህን ሁለት ነገሮች ካፈረሱ ማለትም ያ የተናገሩት ነገር ካልተፈጸመ ወይም ያሉት ነገር ቢፈጸምና እነርሱ ግን እግዚአብሔርን በመተው ሌሎች አማልክትን በማምለክ ሌሎችንም ለማስመለክም ቢያነሳሱ በድንጋይ ተወግረው የመገደል ፍርድ ይጠብቃችዋል። (ሕዝ.13፤ ዘዳ.18:20-22)

3. ለአንድ ወቅትና ቦታ ወይም ሰውና ጉባዔ የሚሆንን መልእክት ግልጽና የማያሻማ በሆነ መንገድ እና ቋንቋ መናገር፤ ይህ መልእክት ማሳሰቢያ፥ ተግሳጽ፥ ማጽናኛ ወይም ምክር ሊሆን ይችላል። ይህ በአንድ የተወሰነ ወቅት ወይም በተወሰነ ስፍራ ላይ የተመሰረተ ከአንድ ሁኔታም ጋር የተቆራኘ በዚያ ጊዜ ብቻ የሚነገርና በየጊዜውና በየቦታው ተደጋግሞ የማይነገር መልእክት ነው። ደግሞም እግዚአብሔር አንድን እውነት በገለጠለት በማንም ሰው ሊነገር

ይችላል ማለትም በአንድ ሰው ብቻ ላይነገር ይችላል። (1ቆሮ.14:31) እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ አለ፤ ይኸውም ትንቢት የመናገር ስጦታና የነቢይነት አገልግሎት አንድና ሁሌም ተመሳሳይ የማይሆኑበትን ሁኔታ አዲስ ኪዳን ይገልጥልናል። ነቢያት ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሰባኪዎች ወይም አስተማሪዎች የተሰጡ ሲሆኑ ትንቢት መናገር ግን መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለአማኝ የሚሰጠው ስጦታ ነው። (1ቆሮ.12 እና ኤፌ.4)

> ከሐዋርያት ትምህርት እንደምንረዳው በነቢይነት አገልግሎትና በትንቢት ስጦታ መሃል የተሰመረ ግልጽ መስመር አለ። ምንም እንኳ ከመንፈስ ቅዱስ ቅባት የተነሳ ሁሉ ሊተነብዩ ቢችሉም ሁሉ ግን ነቢያት አይደሉም። ምንም እንኳ ሁሉ የትንቢትን ስጦታ መግለጥ ቢችሉም ሁሉ ግን ለነቢይነት አገልግሎት የተሾሙ አይደሉም። (1ቆሮ.12:7፥28 እና 29 እንዲሁም 14:29-33 ይመለከቷል) ጳውሎስ በቂሳርያ ከወንጌላዊ ፊልጶስና በቤቱ ከነበሩ አራት ደናግል ልጆቹ ጋር በነበረ ጊዜ አጋቦስ ወደዚያ መጣ። እኒህ አራት ደናግል የትንቢት ስጦታ ቢኖራቸውም እንኳ አጋቦስ ነበር የነቢይነት አገልግሎት የነበረው። አራቱ ደናግል ሳይሆኑ አጋቦስ ነበር ስለ ጳውሎስ ተላሚ ትንቢት ሰጥቶ የነበረው።[3]

እንዲህ የሚነገሩ ትንቢቶች ሁሉ በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው። ተናጋሪዎቹ ሰዎች በመሆናቸው ሊስቱም ይችላሉና እነርሱም ሆኑ አድማጮቻቸው ጠንቃቃዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

4. የእግዚአብሔርን የተገለጠ ፈቃድ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን መግለጥ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁለት ታላላቅ የአገልግሎት ዘርፎች ነበሩ። እነዚህም የክህነትና የነቢይነት የአገልግሎት ዘርፎች ናቸው። የክህነት አገልግሎት በኋላ በአንድ ነገድ ማለትም በሌዊ ብቻ እና በቤተ መቅደስ ዙሪያ የሚሽከረከር ሲሆን እግዚአብሔር ነቢያትን ከተለያዩ ነገዶች በማስነሳት በተለያዩ ቦታዎችና ሁኔታዎች ውስጥ እንዲያገለግሉ አድርጓል። የነቢያት ልጆች ወይም የነቢያት ጉባዔ የሚባል ነቢያት ተሰባስበው የሚማሩበት ትምህርት ቤት መሰል ነገርም በብሉይ ኪዳን ዘመን ነበር። (1ሳሙ.10:5-13፤ 2ነገ.2:1-18) እነዚህ የተሰባሰቡ ነቢያት ምናልባት ከአንጋፋ ነቢያት ትምህርትን በመቅሰም ይሰለጥኑና የእግዚአብሔርን ቃል ይማሩ ይሆናል። ሕዝቅኤል ከካህናት ወገን ሆኖ በነቢይነትም ያገለገለ ሰው ነበር። የነዚህ ነቢያት ተቀዳሚ ስራቸው ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማሳወቅ፥ መምከር፥ ሲያጠፉ መገሰጽ፥ ከእግዚአብሔር ሕግ ሲወጡ ማስጠንቀቅና ወደ መስመር መመለስ ነው።

በአዲስ ኪዳንም ጌታ ነቢያትን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ምዕመናን የእግዚአብሔርን አሳብ እንዲያውቁና እንዲያገለግሉም ነው።

> ሁለቱም ማለትም የብሉይ ኪዳን ነቢያትና በመጠኑም የአዲስ ኪዳንም ነቢያት የመግለጥ አገልግሎት ስለነበራቸው ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ እውነትን በመቀበል አስተላልፈዋል። (ይህም) በተጻፈው ቃል ምትክ የሆነና ያንን የሚናገሩበትን ጉዳይ ወይም ነገር የተመለከተ ነው። እኔ እንደማየው የዘመናችን የትንቢት ስጦታ አዲስ መገለጥን ማስተላለፍ አይደለም ነገር ግን የተጻፈውን መገለጥ ማብራራትና ከሕይወት ጋርም ማዛመድ ነው።[4]

የእግዚአብሔር ፈቃድ በግልጽ የተጻፈው በቃሉ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ቃሉ ትንቢት ተብሎም ተገልጧል። (2ጴጥ.1:20-21) በዘመናችን አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አይጻፍምና የነቢይነትን አገልግሎት የሚያገለግሉት ይህን የተፃፈ ቃል በመግለጥ መሆን አለበት። የሚናገሩትን ቃል ወይም ትምህርት እንደ ኢሳይያስ ወይም እንደ ዮሐንስ ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ መሳይ ስልጣን ያለው ከቶ አይደለም። አለው የሚሉ ካሉ እነዚህ አደገኛ አሳቾች ናቸው።

የትንቢትን አገልግሎት ስናስብ ማስተዋል ያለብን ነገሮች አሉ። ከላይ ከተዘረዘሩት የትንቢት አራት ትርጉሞች የትኛው መሆኑን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ትንቢት በትምህርትና በመግለጥም ይሁን ወይም ሰዎች "...ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" እያሉ ይናገሩት ሁሉንም በጥንቃቄና በማስተዋል መመዘን አለብን። (1ቆሮ.14:29) ተናጋሪዎቹ ሰዎች መሆናቸውንና ሊሳሳቱ የሚችሉ መሆናቸውን አንዘንጋ። ትንቢት በሚነገርበት ወቅት መናፍስትን የመለየት ስጦታ በተግባር ላይ መዋል ይኖርበታል። እያንዳንዱም ምዕመን በውስጡ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእውነተኝነቱን ወይም የእርግጠኝነቱን ምስክርነት ማስተዋል አለበት እንጂ የተነገረውን ሁሉ ያለ ጥያቄ መቀበል የለበትም። ትንቢት ተናጋሪዎችም በአንፃሩ የተነገረውን ነገር ሰሚዎች እንዲቀበሉ የፍርድን ነገር በመናገር ማስፈራራት የለባቸውም። ይህን ማለት ያስፈለገው በመጽሐፍ ቅዱስ "ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና" ተብሎ የተፃፈውን ለማስገንዘብ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ ከሐሳዊ ነቢያት መጠበቅና መጠንቀቅ አለበት። የሚነገሩ ትንቢቶችን ከቃሉ ጋር ያለመጋጨታቸውን ማስተዋል ተገቢ ነው። ለዚህም ደግሞ የጌታን ቃል ማወቅ የአንድ ክርስቲያን ኃላፊነቱና ሕይወቱን የመጠበቅ ግዴታውም ጭምር ነው። የተናጋሪዎቹ ሕይወት ደግሞ ቁልጭ ተደርጎ መታየት አለበት። በስሙ አጋንንት አውጥተው፥ ትንቢት ተናግረውና

ተአምራት ሰርተው "አላወቅኋችሁም" የተባሉ አሉና ዛፍ ከፍሬዋ እንደምትታወቅ ነቢያትም ከፍሬአቸው ይታወቃሉ። (ማቴ.7:22-23)

ሌላው ማስተዋል ያለብን ትንቢትን መናቅ እንደሌለብን ነው። (1ተሰ.5:21) የተነገረውን ምክር ወይም ተግሳጽ ሁሉ የሰው ወይም የሰይጣን ነው ብሎ በደፈናው መወሰንም ስህተት ነው። ጌታ ሊናገር የወደደውን ሲናገር 'የጌታ አይደለም' ካልን ላለመታዘዝ ልባችን ይከፋላል። ትንቢትን ሳንንቅ ማስተዋል አለብን። የትንቢት ስጦታ ወይም የነቢይነት አገልግሎት የተሰጣቸው አማኞችም ማናቸውም አገልጋዮች እንዲሆኑ የሚጠበቅባቸውን ሆነው መገኘት አለባቸው። እነዚህ አገልጋዮች ለጉባኤ የሚያመጡት መልእክት ተቀባይነትን እንዲያገኝ የስጋና የስሜት ጉልበት እንዳይጨምሩበት ያሻል። ስህተቶች ከተፈጸሙም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሩን በጥሞናና በጸሎት ሆነው በማጤን ከስጦታዎች ሁሉ በሚበልጠው በፍቅር በመቅረብ እውነትን በመያዝ ሊያርሙና ሊያስተካከሉ ኃላፊነት አለባቸው።

## የማገልገል ወይም የዕርዳታ ስጦታ

በሮሜ.12:7 እና በ1ቆሮ.12:28 የተጠቀሱት ቃላት ተመሳሳይ ባይሆኑም ትርጉማቸው ግን አንድ በመሆኑ ይህ ስጦታ አንድ ስጦታ መሆኑን እንረዳለን። ሮሜ.12 ውስጥ የተጠቀሰው 'አገልግሎት' የሚለው ቃል ዲያቆን የሚለው ቃል የተሰራበት ነው። ዲያቆን ማለት አገልጋይ ማለት ነው። ይሁን እንጂ የዲቁና አገልግሎትና የማገልገል ስጦታ የተለያዩ መሆናቸው መታወቅ አለበት። የዲቁና አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት ሹመቶች አንዱ ነው። ዲያቆናት የዲቁና ማለትም የማገልገል ስጦታ ከኖራቸው ውብ ነገር ነው።

የማገልገል ወይም የዕርዳታ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ከጉልበት ስራ አንስቶ እስከሰለጠነ የአዕምሮ ስራ ድረስ ማናቸውም ዓይነት ዕርዳታ ቢያስፈልግ ጊዜን፥ ጉልበትን፥ ገንዘብን፥ ዕውቀትን፥ ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ በመሰዋት ለማገልገል መፍቀድ ማለት ነው። ይህ አገልግሎት ለሌሎች አገልግሎቶች በተሟላ ሁኔታ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ትልቅ አስተዋፅዖ የሚያበረክት የአገልግሎት ክፍል ነው። የሞተር ዘይት የሚሽከረከሩት የመኪናው ክፍሎች ያለ ፍትጊያና ያለ መጩነቅ እንዲሽከረከሩ የሚያደርገውን ያህል የማገልገል ወይም የእርዳታ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ሌሎች አገልግሎቶች ያለብዙ ችግርና ጫና እንዲከናወኑ ያደርጋሉ።

በ1ቆሮ.12:28 የተጻፈው 'እርዳታ' የሚለው ቃል ማገልገል ማለት ሆኖ በተለይ ማገዝ ወይም ሸክምን መሸከም እንደማለት ነው። በሐዋ.20:35 "ድውዮችን ልትረዱና" በሚለውና በሮሚ.8:26 "መንፈስ ድካማችንን ያግዛል" በሚለው ውስጥ ያሉት ቃላት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ናቸው። አሳቡም ተመሳሳይ ነው የሌላውን ሸክም መቀነስ ሌላውን ማገዝ ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት የተመረጡበት ዓላማ ሐዋርያትን ለማገዝ ነበር ማለትም የነርሱን የአገልግሎት ሸክም ለማቃለል ነበር። ሐዋርያት በቃሉና በጸሎትም እንደገና ደግሞ በማዕድም እያገለገሉ ፋታ እንዳያጡ ነበር የተመረጡት። ዲያቆን የሚለውን ቃልና የማገልገልን ስጦታ አሳብ መመሳሰል ሐዋ.6:1-6 ይገልጠዋል።

ይህ አገልግሎት በሹመትም ይሁን በስጦታ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በብዙዎች ዘንድ በየዕለቱ የሚደረግና የሚታይ አገልግሎት ነው። በየጊዜውም ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ የሚያጋጥመንና የድርሻችንን ልንወጣ ከፊታችን የሚደቀን አጋጣሚ መሆኑን አውቀን አማኞች ሁሉ ይህን ዕድል ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀምበት ንቁዎች መሆን ያሻናል።

## የማስተማር ስጦታ

ይህ ስጦታ በሮሜ.12:7፤ በ1ቆሮ.12:28-29 እና በኤፌ.4:11 ተጠቅሷል። በመጀመሪያዎቹ በሁለቱ ጥቅሶች ስጦታው በተለይ ማስተማርን ሲሆን በሦስተኛው ጥቅስ ደግሞ ስጦታው የተሰጠው ሰው ራሱ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ስጦታ ተደርጎ መሰጠቱን ያሳያል። በኤፌ.4:11 "መጋቢዎችና አስተማሪዎች" የሚለው ሐረግ ለየብቻ እንደ ሁለት የተለያዩ ስጦታዎች ወይም ሁለቱም ስጦታዎች እንዳሉት አንድ ሰው ማለትም እንደሚያስተምር መጋቢ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህኛው ማስተማር ለመጋቢ የተሰጠ ስጦታ እንደሆን ቢመስልም በሌሎቹ የስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ የማስተማር ስጦታ በግልጽ ተጽፎ መገኘቱ እውን ነው።

የማስተማር ስጦታ ያላቸው አማኞች ያላቸው ልዩ ችሎታ የተገለጠውንና የተፃፈውን የእግዚአብሔር ቃል ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን ግልጽ በሆነና ከሕይወት ጋር በሚዛመድ መንገድ ለሰዎች በሚገባ ቋንቋ ማስተማርና ማስረዳት ነው። አዲስ መገለጥ ፈጽሞ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የታተመና የተዘጋ መጽሐፍ ነውና የመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ ከበቃበት ጊዜ

እንስቶ አዲስ መገለጥ የለም። አይኖርምም። መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ካስፃፈው ቃል ጎን ወይም ቀጥሎ የሚሆን አዲስና እኩያ መገለጥን አይሰጥም። ነገር ግን ቀድሞ የተጻፈውን ያብራራዋል። ይበልጥ ለማብራራትም ይህ የማስተማር ስጦታ ያላቸውን ክርስቲያኖች አገልግሎት ይጠቀማል።

የማስተማር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች አገልግሎት እግዚአብሔር እንደወደደ የተለያየ ዓይነት ዝንባሌና ባህርይ ያላቸውን ሰዎች ለመድረስ ሊጠቀምበት ይችላል። ለምሳሌ ወጣቶችንና ሕፃናትን ለማስተማር የተለያዩ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶችን መቅረጽና ማንቀሳቀስም ሊሆን ይችላል። ማስተማር እንደ ስብከት የአጭርና የጥቂት ጊዜ አገልግሎት አይደለም። አያሌ ቀናትና ሳምንታት እንዲያውም ወራትና ዓመታትም የሚጠይቅ አገልግሎት ነው። ስብከትን የእዳሪ እርሻ ማሳን እንደመሰንጠቅ ብንወስደው ማስተማርን እንደማለስለስ ልንወስደው እንችላለን። ወይም ስብከትን እንደ መዝራት ብንወስደው ማስተማርን እንደ ማጠጣትና መኮትኮት ልንወስደው እንችላለን። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ከተከለ በኋላ በነዚያ ቦታዎች ብዙ ወራትና አንዳንዴም ዓመታት እያስተማረ ይቆይ ነበር። ጌታችንም ሐዋርያቱን ለማስልጠንና ለማሰማራት ከሦስት ዓመታት በላይ አስተምሯቸው ነበር። አንድ ቦታ ተተክሎ ብዙ ጊዜ መቆየት የአስተማሪዎች አንድ ባህርይ ነው።

የአንጾኪያዋ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሰዎች የዳኑባት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በርናባስም ያገለግልባት የነበረች ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በዚያን ጊዜ በርናባስ ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ ሄዶ አግኝቶ ይዞት ተመለሰ። ሁለቱም ለአንድ ሙሉ ዓመት በቤተ ክርስቲያን በመሰብሰብ አስተማሩ። በርናባስ የሳውልን ስጦታ ያስተዋለ ይመስላል። (ሐዋ.11:25-26) ጳውሎስ በኤፌሶንም ሦስት ዓመታት በመቆየት አስተምሯቸው ነበር። (ሐዋ.20:21-22 እና 31)

ይህ ስጦታ ብዙ በክርስትና ሕይወት ውስጥ እየተማሩ በመቆየት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ተምሮ በመመረቅ የሚገኝ አይደለም። እንዲህ ማለት ግን የማስተማር ስጦታ ያለው ሰው ከመንፈሳዊ የትምህርት ተቋሞች የራቀ ሰው መሆን አለበት ማለት አይደለም። እንዲያውም ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል በትክክልና በንጽህና ወደሚስተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች በመግባት የተወሰኑ ጊዜያት ቢማሩ ለመንፈሳዊ ጉዟቸውም ሆነ ለአገልግሎታቸው ይረባቸዋል እንጂ ኪሳራ አይሆንባቸውም። በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የግድ መኖር አለበት። በአንድ በኩል ወይም በሌላ የሚሰጥ ትምህርት የግድ መኖር አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መልክ ይሁን በሰንበት ትምህርት፥ በቡድን ሥልጠና ይሁን በማታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ብቻ በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ ትምህርት መኖር አለበት። ትምህርት እንዲሰጥ የማትተጋ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ስህተቶች ለመጠቃት የተጋለጠች ቤተ ክርስቲያን ናት። ሐዋርያት ወይም የወንጌል ሰባኪዎች ለዳኑትም ላልዳኑትም ሊሰብኩ ይችላሉ፤ መጋቢዎችና አስተማሪዎች ግን ስጦታቸው የዳኑትን መመገብና ማስታጠቅ ነው።

ሁሉ አስተማሪዎች አይደሉም፤ (1ቆሮ.12:29) መሆንም ደግሞ የለባቸውም። (ያዕ.3:1) ነገር ግን የሆኑ አሉ። ቤተ ክርስቲያን ስጦታው ያላቸውን ማወቅና በመስካቸው ሆነው ያገለግሉ ዘንድ ማመቻቸት አለባት። ቤተ ክርስቲያን የቃሉ ትምህርት ቤትም በመሆን አማኞች ቃሉን እንዲያጠኑና በጥልቀት እንዲመረምሩ የምትመች መድረክ ልትሆን ያስፈልጋል። በልዩ ልዩ ርዕሳዊ መንፈሳዊ ትምህርቶችና በመሳሰሉትም ክርስቲያኖች የሚታነጹበትን ዝግጅቶች ልታሰናዳ ኃላፊነት አለባት። ምዕመናንም ይህ ስጦታ ያላቸውን አገልጋዮች ለይቶ በማወቅ በጉባዔም ይሁን በግል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ቃሉን ልንቀስምባቸው ያስፈልገናል።

## የመምከር ስጦታ

ይህን ስጦታ በሮሜ.12:8 እናገኛለን። መምከር ማለት ማጽናናትን፥ ማበረታታትን፥ መገሰጽንና ማረምን የሚሸፍን ሰፋ ያለ ቃል ነው። ዓላማው ጥሩው ነገር እንዲቀጥል መጥፎው ደግሞ እንዲቀር ማድረግ ነው። አዲስ ኪዳን አማኞች እርስ በርሳቸው ማለትም አንዱ ሌላውን መምከር እንዳለበት ይናገራል። እንግዲህ አማኞች ሁሉ የመምከር አጋጣሚ በሚያገኙበት ጊዜ ሁሉ የመምከር ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው። ይሁን እንጂ የመምከር ልዩ ስጦታ ያላቸው አማኞች ደግሞ አሉ።

ይህ መምከር የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ 'ፓራክሌሲስ' ይባላል። ግሱ 'ፓራካሌኦ' ይሰኛል፤ ጰራቅሊጦስ የተባለው ቃል የተሰራውም በዚሁ መነሻነት ነው። ጰራቅሊጦስ ማለት አጽናኝ ማለት ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ከተጠራባቸው ስሞች መካከል አንዱ ነው። (ዮሐ.14:16) ይህ ቃል 'መጠራት' እና 'ከጎን መሆን' የሚል ትርጓሜ ካላቸው ሁለት ቃላት የተመሠረተ ነው። በአንድ ላይ 'ተጠርቶ መጥቶ ከጎን ወይም አብሮ መሆን' እንደማለት ነው። የመምከር አገልግሎት አብሮ ወይም ከጎን የመሆን አገልግሎት ነው። ይህን አገልግሎት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና

መጋቢዎችም ደርበው ሊያደርጉት ይችላሉ። ይህ ማለት እኒህ ሁሉ ስጦታው አላቸው ማለት ባይሆንም የአገልግሎት ኃላፊነታቸው ይህንንም አገልግሎት እንዲደርቡት ያስገድዳቸዋል። ደግሞም መመገብ፥ ማስተማር፣ መስበክና ትንቢት ከዚህ ስጦታ ጋር በመልክ ይቀራረባሉ። ነገር ግን በነጠላ አንድን ሰው ወይም ጥቂት ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ጉባዔንና በርካታ ሰዎችን በአንድ ጊዜ በመምከር ማገልገል እንዲቻል ያደርጋሉ። (1ቆሮ.14:31፤ 1ጢሞ.4:13-14)

በዘመናዊው የሥነ-ልቡና ሳይንስ የሰለጠኑ ሰዎች በዚህ መሰል መስክ በመሰማራት የተለያዩ ዓይነት ለምሳሌ እንደ ጋብቻና ትዳር፣ ወይም በማናቸው የሕይወት ቀውስ በሚከተልበት ጊዜ የምክር አገልግሎትና የመሳሰሉትን የማማከር አገልግሎቶች ይሰጣሉ። የመምከር ስጦታ ያላቸው ክርስቲያኖች ይህን መሰሉን ዓለማዊውን ዕውቀት ስለቀሰሙ ሳይሆን ሰማያዊውን ስጦታ ስለታደሉ በዚህ መስክ ሲያገለግሉ መሰማትና ሞገስ አላቸው። ደግሞም የስጦታው ምንጭ እግዚአብሔር ነውና ውጤቱ በበረከት የተሞላ ነው። እነዚህ ይህ ስጦታ ያላቸው አማኞች በእግዚአብሔር ቤት ብዙ በኖሩ፥ በቃሉም ብዙ እያደጉና በአገልግሎቱም ብዙ እየጠለቁ በሄዱ ቁጥር ደግሞ ይህ ስጦታ ይበልጥ እንደሚቆነጅ ግልጽ ነው። ይህ ስጦታ ያላቸው ወገኖችም ከጸጋው ስጦታም ሆነ ከመንፈስ ቅዱስ አሰራር የተነሳ ሌሎችን የመቅረብና ምክርን የመለገስ ችሎታ አላቸው፤ የዚህኑ ያህል ደግሞ ምስጢርን የመቋጠርና ታማኝ የመሆን ኃላፊነትም ይጠበቅባቸዋል።

## የመስጠት ስጦታ

ይህም ስጦታ በሮሜ.12:8 እንዲሁም እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ ጸጋ በ2ቆሮ.8:1 ተጠቅሷል። ማንም ክርስቲያን መስጠትን በተመለከተ መወጣት ያለበት ድርሻ አለ። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎች በኩራትን (የመጀመሪያ ፍሬን)፥ አስራትን (ከማናቸውም ገቢ አንድ አስረኛን) እና መባን (የፈቃድ ስጦታን) ይሰጡ ነበር። ከዚህም ሌላ ስዕለትንም ለእግዚአብሔር ይሰጡ ነበር። በአዲስ ኪዳንም ክርስቲያኖች ከፍቅርና ከፈቃድ የተነሳ ከእግዚአብሔርም ውለታና ለቤቱ ሥራ ከመታዘዝ የተነሳ ይሰጣሉ። በመስጠት ማገልገል ሁሉም አማኞች የሚጠበቅባቸው አገልግሎት ነው። ነገር ግን መስጠትና መለገስን ይበልጥ የመውደድና የማድረግ ስጦታ ያላቸው ክርስቲያኖች ደግሞ አሉ።

እነዚህ የመስጠት ስጦታ ያላቸው አማኞች ገንዘባቸውን የሚሰጡት የእግዚአብሔርን ስራ በምድር ላይ ለምታንቀሳቅሰው ለቤተ ክርስቲያን ወይም ወንጌል ለሚያሰራጩና ቅዱሳንን በመንፈሳዊ ረገድ ለሚያስታጥቁ የቤተ ክርስቲያን ተጓዳኝ ድርጅቶች ወይም ወንጌልን ለሚያሰራጩ ሚስዮናውያንና ወንጌላውያን አገልጋዮች ወይም በችግር ላይ ለሚገኙ ለሚያገኟቸው ሰዎች ወይም ለሌላ መሰል አገልግሎት ሊሆን ይችላል። ይህንንም የሚያደርጉት የእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን በሚያነሳሳው መንገድ ነው። "የሚሰጥ በልግስና ይስጥ" እንደተባለ እነዚህ አማኞች ስጦታቸውን በትጋት ሊፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል።

## የመግዛት ስጦታ

ቤተ ክርስቲያን ሕያው ዘአካል (organism) እንዲሁም ተቋም ወይም ድርጅትም ናት። እንደ ዘአካልነቷ መጠን የሁሉ አቀፏም ሆነ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እራስና መሪዋ ክርስቶስ ነው። እንደ ድርጅነቷ ደግሞ አንዷት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም በአንድ አካባቢ የሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ወይም የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ከክርስቶስ በታች የሰው መሪዎችም ያስፈልጓቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ያወጣው በሙሴ አማካይነት ነው። ወደ ከነዓን ያስገባው ደግሞ በኢያሱ መሪነት ነው። ሌሎች መሳፍንትንና አዳኞችን ንጉሦችንና መሪዎችንም አስነስቶላቸዋል።

ጌታም ቤተ ክርስቲያንን ሲመሠርት መሪዎች የሚሆኑ ሐዋርያትንም አሰልጥኖ ነበር። ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ እረኞች፥ ሽማግሌዎች፥ ኤጲስ ቆጶሳት ተብለው የተጠሩ ሰዎች አገልግሎታቸው በከፊልም ቢሆን አገዛዝንም የተመለከተ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከሰጣቸው ስጦታዎች መካከል አንዱ መግዛት ነው።

መግዛት ማለት በዓለም እንደሚደረገው ባለ ስልጣን በመሆን መቀናጣት ማለት አይደለም። መግዛት ማለት በሥን-ስርዓት ማስተዳደርና መምራት ማለት ነው። ማስተዳደርና መምራት ደግሞ ከቢሮ እስከ መስክ ያሉትን ስራዎች ይነካል። ደግሞም መንፈሳዊ ኃላፊነትንም በማከል ከሰዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል። የመግዛት ስጦታ ያላቸው ሰዎች በነዚህ መስኮች በብቃት ማገልገል የሚችሉ አገልጋዮች ናቸው። ውጥረቶችና ችግሮች ባሉባቸውም ቦታዎችና ሁኔታዎችም ውስጥ ባለመናወጥና ብቃት ባለው ሁኔታ ማስተዳደር

ይቻላቸዋል። ይህንን ያገኙት ከታወቀ የትምህርት ተቋም ተምሮ ዲግሪ በማግኘት ሳይሆን ሰማያዊ በሆነ ስጦታ ነው። እነዚህ ሰዎች ከሌሎች ማለትም ከግለሰቦችም ይሁን ከማኅበረ-ምዕመናን ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነቶች መመዘንና በጤናማነት መያዝ ይችላሉ። ይህ ስጦታቸው የሚለካው ደግሞ ከአጥቢያቸውና እንዲሁም ከቤታቸውም ጭምር ነው። ሰው የራሱን ቤት ሊገዛ ባይችል የእግዚአብሔርን ቤት ሊያስተዳድር አይችልም። (1ጢሞ.3:4)

ይህ 'መግዛት' የሚለው ቃል የተሰራበት የግሪክ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም የመርከብ መሪ ማለት ነው። ለምሳሌ በ1ቆሮ.12:28 የተጻፈው "አገዛዝ" እና በሐዋ.27:11 የተጻፈው ቃል ተመሳሳይ ናቸው። መርከብ መምራት ወይም መንዳት ከማስተዳደር ጋር መመሳሰሉ ተግባራዊ መቀራረብን ያሳያል። መርከብ ጸጥ ባለ ባህር ብቻ ሳይሆን በማዕበልና በወጀብ መሃል ልትሔድ የምትገደድበትም ጊዜ አለ። በየትኛውም ጊዜ መሪው የሚኖረው ሚና የጎላ ነው። የመሪ አገልግሎት ከዚህ ጋር በቅርብ ይመሳሰላል። ሮሜ.12:8 ላይየተጻፈው መግዛት የሚለው አሳብ" ከፊት መቆም ወይም መምራት" የሚለውን የሚያመለክት ነው። ይህና 1ጢሞ.3:4 ላይ ያለው ቃል ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። ከፊት መቆም መታየትንና ምሳሌ መሆንን የያዘ ነገር ነው። የመግዛት ስጦታ ያላቸው ሰዎች በቤተክርስቲያን አመራር ላይ በሚሰማሩበት ጊዜ እጅግ ውጤታማና ፍሬያማ አገልግሎት ይኖራቸዋል። ከራሳቸው አገልግሎት ስኬታማነት አልፈውም ለሌሎችም አገልጋዮች በመስከቻው መሰማራት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። በዚህም ደግሞ ማህበሩ እየታነጸና እየተገነባ እራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ያድጋል። በውጤቱም ልክ በመሳ.5:2 በተጻፈው ዓይነት እግዚአብሔር ይመሰገናል ይከብራል።

## የመማር ስጦታ

ይህ ስጦታ በሮሜ.12:8 የተጻፈው ምህረትን የማድረግ ስጦታ ነው።ምህረት ሲባል ይቅርታ ማድረግ ማለት አይደለም። ይቅርታ ማድረግ ስጦታ ሳይሆን የእያንዳንዱ ክርስቲያን ግዴታ ነው። የመማር ወይም ምህረትን የማድረግ ስጦታ ግን የተቸገሩትን ለመርዳት የመራራት ልዩ ስጦታ ነው።አሁንም የተቸገሩትን መርዳት የክርስቲያን ሁሉ ተግባር ቢሆንም ለነዚህ ችግረኞች አብዝቶ የሚጨነቅ ልብ ያላቸው ይህ ስጦታ የተሰጣቸው ክርስቲያኖች ደግሞ አሉ።

የመግር ስጦታ እንደ ልሳን ወይም እንደ ማስተማር የሚሰማ ወይም እንደ ተአምራት የሚታይ የአደባባይ ስጦታ አይደለም። ይህ ስጦታ እንዳለው ምናልባት ከባለ ስጦታውና ከጥቂት የቅርቦቹ በቀር ማንም ላያውቅ ይችላል። ይህ ማለት ስጦታው ጨርሶ አይታወቅም በጉባዔም ውስጥ በአገልግሎት ላይ አይውልም ማለት አይደለም። ቤተክርስቲያን ችግረኞችን ድኩማንን፥ መበለቶችንና ድሃአደጎችን የምትረዳበት አገልግሎት ከኖራት ይህ ስጦታ ያላቸው አማኞች እጅግ ፍሬያማ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበት መድረክ ነው። ብዙ ሰዎች የሚሰቃዩ ሰዎች ያሉበት አካባቢ መኖር አይፈልጉም። ይህ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ግን ከነዚህ ጋር መሆን ደስታቸው ነው። ከታሰሩ፥ ከታመሙ፥ ከተጨነቁ፥ ከተጣሉ ጋር መሆንና ራሳቸውን ከነዚህ ሰዎች ጋር ማመሳሰል ያረካቸዋል። የዚህ ሁሉ ውጤትም የጌታ ክብር ነው።

ይህን ስጦታ የተካኑት አማኞች እንዴት ማገልገል እንዳለባቸውም መመሪያ ተሰጥቷል። ያም "የሚምር በደስታ ይማር" የሚል ነው። ይህ አገልግሎት ብዙ ጊዜ በጭንቅ ላይ ከሚገኙና በአንድ ወይም በብዙ መንገዶች ከተሰቃዩ ወይም በዚያን ጊዜ በመከራ ውስጥ እያለፉ ካሉ ሰዎች ጋር የሚያገናኝ አገልግሎት ነው። እንደዚህ ያሉ ሰዎችን ማግኘትና ማገልገል ብዙ ጊዜ የጨፈገገ እንጂ የበራ ፊት የሚፈጥር አይመስልም። የተደሰተ ልብ ግን ፊትን ያበራል። ችግረኞች ደግሞ በበራ ፊት ሲገለገሉ እራሳቸውም እንደሚደሰቱ ግልጥ ነው። ይህ አገልግሎት ተግባራዊ ማለትም በተግባር የሚገለጥ ምስክርነት ነው። ተግባር ሲባል በቃል አይገለጥም ማለት አይደለም። ዶርቃ ምናልባት የዚህ ዓይነት አገልጋይ ሳትሆን አትቀርም። (ሐዋ.፱:36-39)

## ጥበብን የመናገር ስጦታ

1ቆሮ.12:8 "ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና" ይላል። ይህ ስጦታ በአንድ ቦታና ወቅት ለሚደርስ አንድ ጥያቄ ወይም ችግር መልስ ወይም መፍትሔ የሚሆንን ነገር ማመንጨትና ተግባራዊም የሚሆንበትን መንገድ መጥረግን የያዘ ስጦታ ነው።

ጥበብ ሲባል ብዙ ዓይነት ጥበብ መኖሩ እሙን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን ብቻ እንኳ የሰው ጥበብ አለ፤ ሰይጣናዊ ጥበብ አለ፤ አንድ ሰው ጌታን ሲያገኝ የሚያገኘው መንፈሳዊ ጥበብም አለ። ይህ ጥበብን የመናገር ስጦታ የሚባለው ግን ከነዚህ ሁሉ የተለየ ነው። አንድ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ሰብዓዊና ሰይጣናዊ የሆነ ጥበብ ሊኖረው ይችላል። አንድ ክርስቲያን ደግሞ

ሰብዓዊና መንፈሳዊ ጥበብ ሊኖረው ይችላል። ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ ግን ጥበብን የመናገር ስጦታ አላቸው ማለት አይደለም። ጥበብን መናገር መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለአማኞች ከሚሰጠው የጸጋ ስጦታዎች አንዱ ነው። ይህ ጥበብን የመናገር ስጦታ መንፈስ ቅዱስ አንድን ወቅታዊ ጉዳይ ለመፈጸም በተአምር የሚያደርገው ነገር ነው። ጉዳዩ አንድን ጥያቄ መመለስ፥ አንድን ዕቅድ መተግበር፥ አንድን የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸም ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል።

ከብሉይ ኪዳን ነቢዩ ዳንኤልና ንጉሡ ሰለሞን ጠቢባን እንደነበሩ ቃሉ ይነግረናል። በተለይ ሰለሞን ይህን ጥበብ ስለለመነ ነበር እግዚአብሔር የሰጠው። (1ነገ.3) ሕፃኑን ለእናቲቱ እንዲሰጥ ያደረገው በዚህ ጥበብ አማካይነት ነበር። ጌታችንም ይህን መሳይ ጥያቄዎችን ሲጠየቅ ይሰጣቸው የነበረው መልስ ተራ መልስ አልነበረም። (ለምሳሌ ማቴ.21:23-27 እና 22:15-22)

እግዚአብሔር ይህን ስጦታ ለአንድ አማኝ ወይም ለአንድ የተወሰነ ጊዜና ቦታ ብቻም ሊሰጥ ይችላልና ያንን ሰው እንደ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ያዥ ወይም እንደ ባለ ዋና ቁልፍ በረኛ መመልከት ተገቢ ላይሆን ይችላል። ጌታን የማያውቁ ሰዎች ለጠንቋዮች የሚሰጡትን ዓይነት ግምት ለነዚህ ሰዎች መስጠት የለብንም። ለአንድ ጥያቄ ጌታ መልስን ሊሰጥ ከወደደ በወደደው ሰው ወይም በፈለገው መንገድ ሊሰጥ ይችላል።

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይህ ስጦታ ሲገለጥ ብዙ ታስቦበት፥ ተጸልዮበት፥ ተወጥቶና ተወርዶ የሚገኘን ለውሳኔ የሚያደርስ አሳብ መለኮታዊ በሆነ መንገድ ለዚያ ስጦታው ላለው ሰው እግዚአብሔር ሲያሳየው ማለት ነው። በሌላ መንገድ ይህ ስጦታ ጥያቄዎችን፥ ችግሮችንና እንቆቅልሽ የሆኑ ውስብስቦችን ከእግዚአብሔር አቅጣጫ ሆኖ እንደማየት ነው። ይህ ስጦታ ብዙዎችን ጥያቄዎች የሚመልስ ሊሆን ይችላል። ጥያቄዎቹም መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆኑ ማኅበራዊ፥ ግብረ-ገባዊ፥ ቤተሰባዊና ምጣኔ-ኃብታዊና መሰል ጉዳዮችን ቤተ ክርስቲያን ወይም ምዕመናን እንዴት መሳተፍ ወይም መጋፈጥ ወይም ማለፍ እንዳለባቸው ሊያመለክትም ይችላል።

# ዕውቀትን የመናገር ስጦታ

"ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል።" (1ቆሮ.12:8) ይህ ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ለአንድ አማኝ የሚሰጠው በሌላ መንገድ ሊታወቅ የማይችልን ነገር እንዲያውቅ የሚያደርገው ስጦታ ሲሆን ዕውቀቱ አንድ ነገርን፥ ምዕመንን፥ ሁኔታን ወይም መሰል ነገሮችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

ይህ ስጦታ እንደ ጥበብ ሁሉ ዓይነቱ ብዙ ነው። ሰብዓዊ ዕውቀት አለ ይህ በደመ-ነፍስና በተፈጥሮ የምናገኘው ዕውቀት ነው። ትምህርታዊ ወይም አካዳሚያዊ ዕውቀትም አለ፥ ይህ ደግሞ አንድ ሰው ወደ አንድ የሆነ የትምህርት ተቋም ገብቶ የሚቀስመው ዕውቀት ነው። ሰይጣናዊ ዕውቀትም ደግሞ አለ፥ ለምሳሌ ጠንቋዮችና ሌሎችም መሰል ሰዎች የምስጢር ዕውቀታቸውን የሚቀዱት ከሰይጣናዊ ቆሻሻ ኩሬ ነው። ሰይጣን መንፈስ ነውና ሰው በአዕምሮው ከሚያውቀውና ከሚረዳው የበለጠ ያውቃል። ከነዚህም ባሻገር መንፈሳዊ ዕውቀት ደግሞ አለ፥ አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን ለዓለም ሞኝነት ቢመስልም ድንቅ የሆነ ዕውቀትን አግኝቷል። ማንም የዓለም አዋቂ በምርምሩ የማያውቀውን ሰማያዊ ዕውቀት ገና ለጋ የሆነው ክርስቲያን ያውቀዋል። ይህ መንፈሳዊ ዕውቀት ነው የሚገኘውም በክርስቶስ ውስጥ ተሰውሮ ነውና ማንም ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ሊያገኘው አይችልም።

ዕውቀትን የመናገር ስጦታ ግን ከነዚህ ሁሉ የተለየ ነው። ዕውቀትን መናገር የሚቻለው ለአንድ ክርስቲያን ለወቅቱና ለቦታው አንድን በሌላ በምንም መንገድ የማይታወቅ ነገርን መንፈስ ቅዱስ ሲያሳውቅ ነው። ይህ ነገር የተሰወረ የሚጎዳ ነገር ሆኖ ያልታወቀ ነገር ወይም ሌላ መሰል መደረግ ያለበት ጠቃሚ ነገር ወይም መቅረት ያለበት ጎጂ ነገር ሊሆን ይችላል። ይህ ነገር ባይታወቅ ኖሮ ምስጢር ሆኖ የሚቀር ነገር ነበር ማለት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜና ቦታ የደበቃቸውን ነገሮች እንዲታወቁ ያደረገበትን ምሳሌዎች እናገኛለን። ለምሳሌ፤

- ሳኦል ሊቀባ ሲፈለግ ዕቃ ውስጥ መደበቁ ታወቀ፤ (1ሳሙ.10)

- የጠላት የጥቃት ዕቅድ ታወቀ፤ (2ነገ.6)

- የሐናንያና ሰጲራ የምስጢር ስራ ታወቀ፤ (ሐዋ.5)

- የሳምራዊቱ ሴት ድብቅ ሕይወት ታወቀ፤ (ዮሐ.4)

እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው ማንነቱን ሊገልጥና የሕዝቡን ህልውናና ንጽህና ሊጠብቅ ነው እንጂ ይህ ስጦታ የተሰጠው ሰው ምስጢር ገላጭ በመምሰል የነሲብና የቃልቻ ስራ እንዲሰራ ከቶ አይደለም። አንዳንድ ክርስቲያኖች ቀድሞውኑ ያወቁትን ነገር ቀድሞ እንዳላወቁትና ግን እንደታወቃቸውና እንደተገለጠላቸው በማስመሰል እየተናገሩ ሰዎችን ያውካሉ። ውጤቱም መፍረስ እንጂ መታነጽ አይሆንም። ይህ ስጦታ የሰዎችን ምስጢርና አሳብ ማወቂያ የአንጎልና የልብ ማንበቢያ ሳይሆን እግዚአብሔር በፈቃዱ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ውስጥ የሚገኙ ምዕመናንን ለማነጽ የሚሰጠው ዕውቀት ነው። አንዳንድ አገልጋዮች ይህን ስጦታ ከፈውስ አገልግሎትና ከራሱ ከመፈወስ ስጦታም ጋር ያቀራኙታል። አንዳንዶችም እንዲህ በማድረግ በእግዚአብሔር ስም በመላ ምትና ራሳቸው የመሰላቸውን ሲናገሩ ራሳቸውንም ማኀበሩንም ያታልላሉም፤ ያውካሉም። ይህ ስጦታ ከፈውስ ስጦታ ጋር ብቻ መቆራኘት እንዳለበት አዲስ ኪዳን አያስተምርም። በእውቀት ስጦታ ወይም በመገለጥ ስጦታ አንድ በሽታ እንደተገለጠላቸውና ያም በሽተኛ እንደተፈወሰ ይናገራሉ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ገላጭ አምላክ ቢሆንም "የመገለጥ ስጦታ" የሚባል ነገር የለም። የመፈወስ ስጦታ ራሱን የቻለ ስጦታ ነውና ሌላ ምርኩዝ አያሻውም። ስጦታዎች በሙሉ በእያንዳንዳቸው በራሳቸው ሙሉዎች ናቸው። በልሳኖች መናገርም እንኳ ሳይተረጎምም በራሱ ሙሉ ስጦታ ነው። ዕውቀትን የመናገር ስጦታ እግዚአብሔር በወደደው ጊዜና ቦታ እርሱ የፈቀደውን ሊያደርግ የሚጠቀምበት እንጂ እንደ መስበክ ወይም ማስተማር አማኙ ሁሌ የሚለማመደው አይመስልም።

እግዚአብሔር ለአንድ አማኝ አንድን ነገር ቢያሳውቀው ያ ነገር የግድ በጉባዔ የሚነገር ላይሆን ይችላል። ለግለሰብ የሚነገር ወይም ጭራሽ የማይነገርም ሊሆን ይችላል። ያ አማኝ ያወቀውን ነገር ማስተላለፍ ከኖረበት እንዴት ማድረግ እንዳለበት መጸለይና ጥበብን መፈለግ አለበት። እግዚአብሔር አንድን ነገር ከገለጠለት ደግሞ ያ ሰው ያ ነገር በእርግጥ የእግዚአብሔር መሆኑን ካረጋገጠ በይሉኝታና በፍርሃት ወይም በመሳሰሉት ነገሮች ተይዞ ዝም ማለት አይገባውም።

# የእምነት ስጦታ

"ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት...።" (1ቆሮ.12:9) እምነት ሲባል ቃሉ ጠቅለል ያለ እውነትን ያቀፈ ነው። እምነት ዓይነት ዓይነት አለው። የክርስትናን እምነት ከወሰድን ሦስት ዘርፎችን ልናይ እንችላለን። የመጀመሪያው ለመዳን ያመንነው እምነት ነው። ይህ ጌታን ያድነናል ብለን እምነታችንን በእርሱ በጣልን ጊዜ እርሱንም በተቀበልን ጊዜ ያመንነው እምነት ነው። የዳንነው በጸጋው አማካይነት በእምነት ነው። (ሐዋ.16:31፤ ኤፌ.2:8)

ሁለተኛው ከዳንን በኋላ ዘየቀኑ የምንኖረው የታማኝነት ኑሮ ነው። በቃሉ ይህም እምነት ተብሏል። ይህ ከመንፈስ ፍሬ ውስጥ የሚገኘው እምነት ነው። አንድ ክርስቲያን ሲድን በእምነት እንደዳነ ሲኖርም በማየት ሳይሆን በማመን መመላለስ ይኖርበታል። ይህ እምነት በየቀኑ ኑሯችን የሚታይና በስራም የሚተረጎም ነው። እምነትና እምነት የሚገለጥበት ስራ የተቆራኙና የማይለያዩ ናቸው። የመጀመሪያው እምነት አማኞች ሁሉ ሲድኑ የፈጸሙት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በየቀኑ ሊኖሩ ከሚጠበቅባቸው ተግባራዊ ክርስትና ጋር የተያያዘ ነው። የዚህ የሁለተኛው እምነት ልቀቱ ከቀን ወደ ቀን እያደገና እየነጠረ የሚሄድ ነው። ይህ በታማኙ አምላክ ማመን ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት መለኪያም ነውና ውበቱ እያደር እየጨመረ የሚሄድ ነው። በማቴ.21:18-22 እንደምናገኘው ጌታ የበለሲቱን ዛፍ ከረገመና ዛፊቱም ከደረቀች በኋላ ዛፊቱ መድረቋን ሲነግሩት የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራቸው ከዚያም የበለጠ እንደሚያደርጉ ነገራቸው። በማቴ.17:14-21 ደግሞ ርኩሱን መንፈስ ሊያወጡ ያልቻሉበትን ምክንያት ቢጠይቁት ስለ እምነታቸው ማነስ መሆኑን ነገራቸው። 'የሰናፍጭ ቅንጣት' ወይም 'ያነሰ እምነት' የሚያመለክቱት ይህ እምነት በባህርይው የሚያድግ እና ልቀቱም እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ነው።

ሦስተኛው ግን ከነዚህ ከሁለቱ የተለየ ነው። ያም የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ የሆነ ነው። ይህ ስጦታ በሁለተኛ ተራ ላይ ያየነው እምነት አድጎ የሚደርስበት የመጠቀ ዕድገት ሳይሆን ራሱን የቻለ ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለተወሰኑ አማኞች የሚሰጠው ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ በአንድ ለማለፍ ከባድ በሚመስልና በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለማለፍ፥ ለመናገር፥ ለማድረግም ልዩ የሆነ መታመንና ድፍረት ማግኘት ነው። በዚያ የከበደ ነገር ውስጥም በእግዚአብሔር ኃይል ቻይነትና አስቻይነት ተደግፎና አርፎ ባለመናወጥ ማለፍ ነው።

በዕብ.11 የምንመለከታቸው ሰዎች እግዚአብሔርን ያስደሰቱበትን እምነታቸውን ስንመረምር፤

- የአንዳንዶቹ አጥቂነትን የሚመስል ነው (ለምሳሌ፤ ጭፍሮችን አባረሩ)
- የሌሎቹ ሽሽትና መከላከልን ይመስላል (ለምሳሌ፤ አመለጡ፥ ተቅበዘበዙ)
- የሌሎቹ ደግሞ ተጠቂነትን ወይም መከራ ተቀባይነትን ይመስላል (ለምሳሌ፤ ተወግረው ሞቱ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ)

በሁሉም ለማለፍ ግን እምነት አስፈልጓቸው ነበር ያለፉትም በእምነት ነበር።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ የጸጋ ስጦታ የሚታየው የትባዔውን መታመን ለማጠንከርና በእምነት ወደተለቀ ደረጃ ለማራመድ ነው። ይህ እምነት በሞኝነት ወይም በየዋህነት አንድ የሌለ ነገርን እንዳለ፥ ያለውንም እንደሌለ መቁጠር አይደለም። አንዳንድ አገልጋዮች የፈውስንና የእምነትን ስጦታ እያደባለቁ ያለ በሽታን እንደሌለ፥ የሌለ ፈውስን ደግሞ እንዳለ በማስመሰል ሰዎች የሆነ ዓይነት የእምነት ጅምናስቲክ እንዲሰሩ ሊያስገድዱ ይሞክራሉ። የዚህ ውጤት አፍራሽና እንዲያውም እምነትን ከመገንባት ይልቅ የሚያወድም ነው። ይህ የእምነት ስጦታ በሚታይ ነገር የሚደገፍ አይደለም ይሁን እንጂ ተፈጻሚና መንፈሳዊ ሕይወትን ገንቢ ነው። ይህ እምነት እራሱ የሚደገፈውም በእግዚአብሔር ቃልና በራሱ በእግዚአብሔር ባህርይ ነው። ኤልያስ ለድርቅ ሳይጸልይ ድርቅ እንደሚሆን አምኖ ነበር። ለዝናብም ሳይጸልይ በፊት ምንም ደመና አልነበረም። ኤልሳዕ ሴቲቱን ባዶ ማድጋዎችን ሁሉ ሰብስባ የነበራትን አንድ ማሰሮ ዘይት በነዚያ ውስጥ እንድትገለብጥ ሲነግራትና ዕዳዋን ልትከፍል በረከትን ሲያውጅላት በእርግጥ አምኖ ነበር። ይህ እምነት አንድን የሆነ ቀመር ሸምድዶና ያንን ተጠቅሞ መለማመድ ሳይሆን በታማኙ መታመንና በእርሱም ማረፍ ነው። እነ ሲድራቅ ወደ እሳቱ የገቡት በእምነት ነበር። ቢፈልግ ደግሞ እንደማያድን ይወቁና ይናገሩ እንጂ አምላካቸው እንደሚያድን ያምኑ ነበር። እምነትን ሁሌ ለኛ ከሚመስለን ተአምር ጋር ማያያዝ የለብንም። የእምነትን ስጦታ ገንቢ ውጤት የምናየው በመጨረሻው ማኅበረ-ምዕመናን ከመታነጻቸውና እግዚአብሔርም የከበረበት ከመሆኑ ላይ ነው።

# የፈውስ ስጦታዎች

"ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ..."(1ቆሮ.12:9) ይህ ስጦታ በተጠቀሰባቸው ቦታዎች 'ስጦታ' ተብሎ በነጠላ ሳይሆን 'ስጦታዎች' ተብሎ ነው በብዜት የተነገረው። ምናልባት በሽታዎች ስጋንና ነፍስንም የሚነኩ ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ይህ ስጦታ እግዚአብሔር ሰዎችን ከስጋዊ፥ አዕምሯዊና ስሜታዊ ደዌና ጭንቀት በማያዳግም ሁኔታ የሚፈውስበት ስጦታ ነው። ይህም ሰዎቹ ፍጹም ጤናማ የሚሆኑበትና አማኞች ደግሞ የሚታነጹበት ለማያምኑ የእግዚአብሔር ህልውና ምልክት የሚሆንበትና እግዚአብሔርም የሚከብርበት ነገር ነው።

ፈውስ በሁለት መንገዶች እንደሚደረግ አዲስ ኪዳን ይነግረናል። የመጀመሪያው በሽተኞች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ይጠሩና ሽማግሌዎችም ዘይት ቀብተው የሚጸልዩላቸው ወይም ምዕመናንም እጆቻቸውን በመጫን የሚጸልዩበት አገልግሎት ነው። (ያዕ.5:14 እና ማር.16:18) በዚህ ጸሎት ላይ እምነት ሊታከልበት እንደሚገባ ግልጽ ሆኖ ተነግሯል። ሁለተኛው ደግሞ የፈውስ ስጦታ በተሰጣቸው ምዕመናን አማካይነት የሚደረገው ነው። እነዚህ አገልጋዮች በአገልግሎታቸው መቼ የትና እንዴት መሥማራት እንዳለባቸው በመጸለይ የጌታን ፈቃድ ማወቅ እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ጋር በመነጋገርና በመጸለይ ለታመሙ የሚጸልዩበት አገልግሎት ነው።

ሕመም ስንል አካልንና አዕምሮን የሚጎዳ ስቃይ ማለታችን ነው። ጌታ ብዙ ድውያንን ፈውሶ ነበር። የአንዳንዶቹ ሕሙማን ሕመማቸው ምን መሆኑ አልተጠቀሰም። ከተጠቀሱት መካከል ግን ሽባ፥ አንካሳ፥ ለምጽ፥ ዕውር፥ ዲዳና ደንቆሮ፥ የሚጥል በሽታ፥ ንዳድ፥ የደም መፍሰስ ይገኙባቸዋል። ጌታ መጀመሪያ 12ቱን በኋላም 72ቱን ሲልካቸው (ሉቃ.9 እና 10) ድውያንንም ይፈውሱ ዘንድ ስልጣን ሰጥቷቸው ነበር። በሐዋርያትም የፈውስ ምልክቶች ተደርገው ነበር፤ ለምሳሌ አንካሳ ተፈወሰ (ሐዋ.3) ሽባ ተነሳ፤ (ሐዋ.9) ከተወለደ ጀምሮ ሄዶ የማያውቅ አንካሳም ተፈውሶ ተመላለሰ። (ሐዋ.14) እግዚአብሔር ባባህርዩም ፈዋሽ አምላክ ነው፤ (ዘጸ.15:26) ስለዚህም ይፈውሳል። ይህ ማለት ግን መፈወስ ግዴታው ነው ማለት አይደለም። የፈውስ አገልግሎት ሲወሳ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ወደጎን መደረግና መዘንጋት የለበትም። ከዘመናችንም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታምመውና ተጸልዮላቸው ያልተፈወሱ ቅዱሳንን ስናስብ ይህንንም አብረን ማጤን ይገባናል።

በዚህ ዘመን የዚህ ስጦታ መኖር እውነት ነው። የዚያኑ ያህል ሰዎች ሲያበላሹትና ያልተሰጣቸውም እየኮረጁ ሲለማመዱት ስለሚታይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አገልጋዩና ታማሚው ሲገናኙ አገልጋዩ ስጦታው እንዳለው ታማሚውም በሽታው እንዳለበት ታማኝ ሆነው መነጋገር አለባቸው። በተለይ አገልጋዩ የፍቅር ስሜት ሊኖረው ይገባል። ይህ ደግሞ ስሜታዊ በመሆን የሌለ ፈውስን እንዳለ መቁጠርና ያልተፈወሰ ሕመምን ደግሞ እንደሌለ መቁጠር አይደለም። የፈውስ ስጦታ ከኖረ ፈውስም አለ ማለት ነው። የተጸለየለትም ሰው ያልተፈወሰ እንደሆነ ሊፈረድበትና ሊኮነን አይገባውም። እምነተ-ጎዶሎም ተደርጎ መንኳሰስ የለበትም። በሽተኛው ካልተፈወሰ ተጠያቂነቱ በአመዛኙ መውደቅ የሚገባው በስጦታው እውነተኛነት ላይ ነው። ከዚህም ባሻገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንነት መስተዋል አለበት። ስጦታው የሌላቸው አገልጋዮች ለሕሙማን ይጸልዩና ሕመምተኞቹ ካልተፈወሱ እነዚህ አገልጋዮች የራሳቸውን እውነተኛነት ከመመርመር ይልቅ የበሽተኞቹን እምነት መመርመር ይቀናቸዋል። በሽተኞቹም ያለመፈወሳቸው ሳያንሳቸው የእምነታቸውን ቁርቁዝና (እምነተ ቢስነታቸውን) ተሸክመው ይመለሳሉ። የነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ቢጎዳ እንግዲህ አያስገርምም። ለዚህ ነው ጥንቃቄ የሚያሻው።

አንዳንዴ በጉባዔ መሟሟቅና የስሜት ግለት ሕሙማን እውነተኝነት የሌለው የፈውስ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ያንንም ስሜት ‘ፈውስ’ ነው ብለው ‘በእምነት’ ለመቀበል መገደድ የለባቸውም። እውነተኛ ፈውስና ውሸታም ስሜት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ፈውስ ከኖረ ለሕመምተኛው ብቻ ሳይሆን ለተመልካችም ጭምር ሊታወቅ ይችላል። የፈውስ ስጦታ ያላቸው አማኞች በሌሎች ዘንድ እንደ ልዩ ተአምር አድራጊዎች ወይም ደግሞ እንደ ምትሃተኞች ሊታዩ ስለሚችሉ በአገልግሎታቸው ወቅትም ሆነ ከዚያ ውጪ የሰዎችን አትኩረት እንዳይስቡ መጠንቀቅ አለባቸው።

## ተአምራትን የማድረግ ስጦታ

ይህ በ1ቆሮ.12:10 የተጠቀሰው ስጦታ መለኮታዊ በሆነ ጣልቃ-ገብነት እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ ኃይሉ የተፈጥሮን ኃይል ሲለውጥና ተፈጥሯዊና ተለምዷዊ ያልሆነን ነገር ሲያደርግ ማለት ነው። ይህ ስጦታ በተግባር ሲውል እግዚአብሔር በዚያ ጊዜና ቦታ ያለውን ተፈጥሯዊ ሕግ ለሁሉ ሳይሆን ለጊዜው ይለውጠዋል ወይም ያቆመዋል። ጌታ ይህ እንዲሆን

የሚያደርገው አንደኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ወይም ቤተ ክርስቲያን ለዚያ ጊዜ ያስፈለጋቸው ነገር እንዲፈጸም እንዲሁም ሁለተኛ የእርሱን ማንነት ለመግለጥ ነው። ተአምራት በተሰሩባቸው ቦታዎች ሁሉ እኒህን ሁለት ነገሮች እናስተውላለን። ስራዎቹ ብዙ ቢሆኑም ክብሩ ግን ተመሳሳይ ነው።

ለምሳሌ ባህር ተከፈለ ማለት ሕዝቡ ተሻገረ፥ እግዚአብሔር ከበረም ማለት ነው። ውሃ ወደ ወይን ተለወጠ ማለት የሰዎች ገበና ተሸፈነ ብቻ ሳይሆን ጌታ ክብሩን ገለጠም ማለት ነው። ሰው ምንም ዕውቀቱ ቢያድግና ቢመጥቅ ተአምራትን መስራት አይችልም። ከተፈጥሮና ከተፈጥሮም ሕግጋት ጋር ይተባበራል እንጂ ሊለውጣቸው ወይም ሊያቆማቸው አይችልም። የተአምራት መኖር የእግዚአብሔርን ማንነት በመግለጥ መንግስቱ እንድትሰፋ ትልቅ አስተዋፅዖ ያደርጋል፤ ይሁን እንጂ ተአምር እምነትን መውለድ እንደማይችል መታወቅ አለበት። ተአምር ያለውን እምነት ሊያሳድግ ይችል እንደሆን እንጂ እምነትን የመፍጠር ችሎታ የለውም። እምነት የሚመጣው ቃልን ማለትም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ብቻ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ተአምራት ተጽፈዋል። አንዳንዶቹ እግዚአብሔር በቀጥታ ራሱ ያደረጋቸው ሲሆኑ ሌሎቹ በሰዎች አማካይነት ያደረጋቸው ናቸው። እኒህን ተአምራት በብሉይ ኪዳን እንዲሁም ከአዲስ ኪዳን በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ እናገኛቸዋለን። ባህር ሲከፈል፥ ምግብ ከሰማይ ሲወርድ፥ ወንዝ ሲቆም፥ ፀሐይና ጨረቃ ሲቆሙ፥ የሞቱ ሲነሱ፥ ውኃ ወደ ወይን ሲለወጥ፥ ማዕበል ፀጥ ሲል ሌሎችም ተደርገዋል። በዕብ.2:3-4 እንደምናገኘው በሐዋርያት ዘመንና በእጃቸው የተደረጉት ድንቆችና ምልክቶች እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር መልእክተኞች የመሆናቸው ማስረጃና ማረጋገጫዎች ነበሩ። ደግሞም በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ገና ተጽፎ አላለቀም ነበርና እነዚህ ነገሮች እንደ ምስክርም በመሆን ያገለግሉ ነበር። ተመሳሳይ አሳብ ከ2ቆሮ.12:12 እናገኛለን። ከዚህም ተአምራት የሐዋርያት የማንነታቸው በተለይም የማን መልዕክተኞች የመሆናቸው ምልክት ሆኖ እናገኘዋለን።

በዘመናችንም እንደነዚህ ያሉ ተአምራት እግዚአብሔር እንደፈቀደ ሊደረጉ ይችላሉ። ከተደረጉ ዓላማቸውን መፈጸምና ግባቸውንም መምታት አለባቸው። በመጨረሻው ዘመን ሐሰተኞች ክርስቶሶች ስለሚነሱና ከእግዚአብሔር ያልሆኑ ተአምራትም ስለሚደረጉ በሰዎች በኩል የሚደረጉ ተአምራት ሁሉ ከእግዚአብሔር ናቸው ብለን መቀበል የለብንም። የሰዎቹ የክርስትና ሕይወትና በነገሩ ውስጥ የእግዚአብሔር ክብር መገለጡ ለማገበሩም ያ ነገር ማስፈለጉና ጥቅሙ አብረው መታየት አለባቸው፤ መለኪያዎቹም ሊሆኑ ይገባል። ተአምራት ሰዎችን ለማዝናናትና ለታይታ የሚደረጉ ነገሮች

አይደሉም። ተአምራትን የማድረግ ስጦታ ከእምነት ስጦታ ጋር ምናልባት ይዋሰን ወይም ይገናኝ ይሆናል። ፈውስን በተመለከተ ደግሞ ፈውስ ተአምራዊ በሆነ መንገድ ሊከሰት ቢችልም ተአምራዊ ባልሆነ መንገድም መዳን ስለሚቻል ከተአምራት ማድረግ ስጦታ ጋር መያያዝ የለበትም። ደግሞም ፈውስ ራሱን የቻለ አንድ ስጦታ ነው።

ከዚህ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወዲህ በተነሳውና "ሦስተኛው ሞገድ" ተብሎ በሚጠራው ንቅናቄ ተአምራት እንደ እውነተኛ የወንጌል አገልግሎት ምልክት ተደርገው ተወስደዋል። በዚህ ንቅናቄ ውስጥ "ሰዎች ተአምራትን ቢያዩ ተአምራትን ሳያዩ በወንጌል ምስክርነት ብቻ ከሚድኑት ይልቅ ብዙ ሰዎች ይድናሉ ደግሞም ተአምራት ካለ እምነት ይኖራል" ተብሎ ይነገራል። ስለዚህ "ሦስተኛው ሞገድ" ስለሚባለው ስህተት በመጠኑ በሌላ ቦታ እናያለን፤ ተአምራት ግን እምነትን የማርገዝም ሆነ የመውለድ ችሎታ እንደሌላቸው እዚህ ቦታ መታወቅ አለበት ቃሉም ይህን ያስተምረናል። ስለዚህ ተአምራት በሚከሰቱበት ወይም ስለ ተአምራት በምንሰማበት ጊዜ ቀዳሚ ዓላማቸውንና በቤተ ክርስቲያን መታነጽ ውስጥ የሚኖራቸውን ተገቢ ሥፍራ በማስተዋል መቀበል ይኖርብናል።

## መናፍስትን የመለየት ስጦታ

ይህ ስጦታ በ1ቆሮ.12:10 የተገለፈ ሲሆን ከተነገሩ ወይም ከተደረጉ ነገሮች ጀርባ ያለው ኃይልና ግፊት ምንጩ ከየት መሆኑን የማወቅ ስጦታ ነው። አንድ መልእክት ሲነገር ወይም አንድ ድርጊት ሲፈጸም ያ ድርጊት ከእግዚአብሔር መሆንና ያለመሆኑን ማወቅ ነው። የተነገረው መልእክት ከእግዚአብሔር ካልሆነ አንድም ከራስ ማለትም ከአእምሮና ከስሜት ገፋፊነት ያለዚያም ደግሞ ከሰይጣን ገፋፊነት ወይም አነሳሽነት ሊሆን ይችላል። ከአእምሮ መመንጨት ማለት የተነገረውን ነገር በአንጎል ብቻ በማውጣትና በማውረድ አስልቶና አስቦ ሳይጸልይበት ወይም እግዚአብሔር ሳያሳስብ 'ቢባል ወይም ቢሆን ትክክል ነው' የሚሉትን ነገር መናገር ነው። ከስሜት መመንጨት ማለት ደግሞ ምንም ሳይታሰብ ሳይስተዋልም ብልጭ ብሎ በሚጠፋ ሞቅታ መሳይ ነገር የደስታ ይሁን የሃዘን፥ የንዴት ይሁን የሌላ በሆነ ስሜት ተገፋፍቶ መናገር ማለት ነው። ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክት አስቀድሞ የታሰበበትም (በአእምሮ ብቻ) በስሜት ገፋፊነት የሚደረግን አይደለም። ይሁን እንጂ ሰዎችን ከአእምሮም ሆነ ከስሜት ውጪ አያደርጋቸውም። ይህን ማለት ተናጋሪዎቹ በዚያን ጊዜ

ጭንቅላታቸው አይሰራም ወይም ስሜታቸውን መግለጥ አይችሉም ማለት አይደለም። የሚያሳዝን ከሆነ ቢያለቅሱ ወይም የሚያስቆጣ ከሆነ ቢቆጡ "ስሜታውያን" መሰኘት አይገባቸውም። ግን ያ መልእክት በእርግጥ ከእግዚአብሔር መሆን አለበት። ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክት ተናጋሪዎቹን ከአእምሮ ውጪ አያደርጋቸውም ማለት እነዚህ ሰዎች ኅሊናቸውን ስተው አይጠፉም በዚያ ጊዜም 'ባዶ' ሆነው እንደ መተላለፊያ መሳሪያ ብቻም አያገለግሉም ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች አዕምሯቸውን አይስቱም ማስተዋላቸውም አይዘጋም። ግን መልእክቱ የሚመነጨው ከራሳቸው አእምሮ መሆን የለበትም ማለት ነው።

ሰይጣን የራሱን ስራ በሽፋን አድርጎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰራ ሁሌም ይፈልጋል። አንዳንዴ የሚያደርጋቸው ነገሮች ፈጽሞ አያስታውቁም። ይህ ስጦታ ግን የግፊቱን ምንጭ ያውቃል። በማቴ.16:23 ያለውን አሳብ የተናገረው ጴጥሮስ ነው አሳቡ ግን የጴጥሮስ አልነበረም። ሰይጣን ጌታ እንዲሞትና እንዲያድነን አይፈልግምና ይህ እንዳይሆን ጣረ። ጌታም የዚህን አሳብ ምንጭ ስለሚያውቅ ሰይጣንንም ገሰጸው። በሐዋ.8:18-24 እና 13:10 ተቀራራቢ ነገር እናያለን። በ1ዜና.21 እንደምናገኘው ደግሞ ዳዊት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቆጠረና በሚያስጨንቅ ቅጣት ተቀጣ። መቁጠሩ አይደለም ጥፋቱ። ለመቁጠርማ ከዚህ በፊት ተደጋግመው ተቆጥረዋል። እግዚአብሔር ራሱም እንዲቆጠሩ ያደረገበት ጊዜም ነበር። ስህተቱ መቆጠራቸው ሳይሆን እንዲቆጠሩ አሳቡን ያፈለቀው ማን መሆኑ ነበር። አንድን አሳብ ጥሩ ስለመሰለ ብቻ መቀበል አይኖርብንም። 'የማን ነው?' ማለትም አለብን። ኢያሱ በገባዖናውያን ሲታለል ባለመጠየቁ ነበር የሳተው። (ኢያ.9:14) ሔዋን ፍሬውን ስትበላ ፍሬውን ነበር እንጂ ያየችው የአሳቡን አመንጪ አላስተዋለችም ነበር። ወደ መጥፎ ቦታ የሚወስድ መንገድ ቅን ሊመስልም ይችላል።

ከሰይጣን የሚመነጨው ማንኛውም አሳብ በንግግርም ሆነ በድርጊት ወደ አደባባይ ሲወጣ ውጤቱ አፍራሽ ብቻ ነው። ለጊዜው ባይመስልም እንኳ የፍጻሜ ውጤቱ የከፋ ነው። በአማኞች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ስለሚኖር ከሰይጣናዊ አሰራርና ስህተት ይጠብቃቸዋል፤ የሰይጣን የሆነውንም ነገር ያውቃሉ። (1ዮሐ.4:18-27፤ 2ቆሮ.2:11) ሰይጣናዊ የሆነውን ነገር መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ሁሉ ያሳውቅ እንጂ ይህ በትክክል እንዲሆን አማኙም በቃሉ ሊተጋ ይገባዋል። የሐሰት ትምህርቶች ቃሉን ተላብሰውና የእግዚአብሔርን መስለው ነውና የሚያታልሉት ጠሊቅ የሆነ የቃሉ ትጋት ያሻል። ርኩስ መንፈስ የእግዚአብሔር የሆነውን እንደሚያውቅ የእግዚአብሔርም የሆኑት በመንፈሱ አማካይነት የሰይጣን የሆነውን

ያስተውላሉ። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ያላቸው አማኞች ግን የሰይጣን የሆነውን ብቻ ሳይሆን የሰው የሆነውንም ነው መለየት የሚችሉት።

አንዳንድ አማኞች ይህ ስጦታ አላቸው ማለት የሚሰጡ ትምህርቶችንና የሚመጡ መልእክቶችን ሁሉ ሳንሱር አድራጊዎች ናቸው ማለት አይደለም። አንዳንድ ሰባኪዎችን ስለምንጠራጠራቸው ወይም ሳያውቁና ሳያስተውሉ የተሳሳተ ነገር ከተናገሩና ያንን ካወቅን የመለየት ስጦታ ያለን እየመሰለን ለማወክ ያለመሞከር ተገቢ ነው። የእግዚአብሔርን ቃልና ሥነ-መለኮትን መማርና መመርመር ጥሩና አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ስጦታ የትምህርት ውጤት ያለመሆኑም በግልጽ መታወቅ አለበት። የሚነገሩ ነገሮችንና መናፍስትንም መመርመር በተለይ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ነው። (1ተሰ.5:21 እና 1ዮሐ.4:1-6) ከ1ቆሮ.14:29 "ሌሎችም ይለዩአቸው" ከሚለው ቃል እንደምንረዳው በአንድ ጉባዔ የአንድን ትምህርት ወይም ትንቢት ትክክለኛነትና ስህተተኛነት መረዳትና መለየት የሚችሉ ከአንድ በላይ ሰዎች እንደሚኖሩ ነው። ይሁን እንጂ የመለየት ስጦታ ከአላፊ ጥርጥር የተለየ መሆኑ መስተዋል አለበት።

## በልሳናት የመናገርና የመተርጎም ስጦታ

"ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል።" (1ቆሮ.12:10) ልሳን ማለት በተለምዷዊው አማርኛ ቋንቋ አንደበት ወይም የመናገሪያ ብልት ማለት ሲሆን በዚህ ክፍልና በጠቅላላውም በአዲስ ኪዳን እንደምናገኘው ግን በአጭሩ ቋንቋ ማለት ነው። በሌሎች ልሳናት መናገር ማለትም በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ማለት ነው። አንድ ሰው በአንድ ቋንቋ ለመናገር ወይ አፉን በዚያ ቋንቋ መፍታት አለበት ያለዚያም ያን ቋንቋ በትጋት መማር አለበት። አፉን ሳይፈታበት ወይም ሳይማር አንድን ቋንቋ ከተናገረ ያን ንግግር ያገኘው ከራሱ ውጪ ከሆነ ሌላ ምንጭ ነው ማለት ነው።

ልሳን ወይም በግሪክ ቋንቋ 'ግሎሳ' የሚባለው ቃል በአዲስ ኪዳን 50 ጊዜያት ተጽፏል። ከነዚህ ውስጥ ከፊል ያህሉ 'ልሳን' ሲሰኙ የቀሩት ደግሞ 'መላስ' (ለምሳሌ፤ ማር.7:33 እና 35፤ ሉቃ.1:64፤ 1ጴጥ.3:10) 'ቋንቋ' (ለምሳሌ ማር.7:33 እና 35፤ ሉቃ.1:64፤ 1ጴጥ.3:10) 'ቋንቋ' (ለምሳሌ፤ ማር.16:17 እና ራዕ.5:9 ወዘተ.) እንዲሁም 'አንደበት' (1ቆሮ.14:9፤ ያዕ.1:26

እና 3:5-8 እና 1ዮሐ.3:18) ተብለው ተተርጉመዋል። ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ቋንቋዎች በተናገሩባቸው ቦታዎች ማለትም በሐዋ.2:4፤ ሐዋ.10:46 እና ሐዋ.19:6 'ልሳን' ተብለው ተጠቅሰዋል። በተረፈ ልሳን የሚለውን ቃል ከምናገኝባቸው የምናገኘው በ1ቆሮ.12-14 ነው። እነዚህም፤

1ቆሮ.12:10፥ 10፥ 28 እና 30

1ቆሮ.13:1 እና 8

1ቆሮ.14:2፥ 4፥ 5፥ 6፥ 13፥ 14፥ 18፥ 19፥ 22፥ 23፥ 26፥ 27 እና 39 ናቸው።

በአዲስ ኪዳን በሌሎች ልሳናት መናገር ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱ መሆኑ ተጠቅሷል። ስጦታው 'በአዲስ ቋንቋ መናገር'፥ 'በሌላ ልሳኖች መናገር'፥ 'በልዩ ልሳን መናገር'፥ 'በሰዎችና በመላእክት ልሳን መናገር' በመባል ተጠቅሷል። ይህን ስጦታ በብሉይ ኪዳን አናገኘውም። በአዲስ ኪዳንም የተለያየ ደረጃ፥ ክፍፍል ወይም ዓይነትነት ያለው ሆኖ አናገኘውም። ሆኖም ግን ከሌሎች ስጦታዎች በአንድ ነጥብ ብቻ ለየት ያለ ሆኖ እናገኘዋለው፤ ያም ስጦታዎች ሁሉ (ልሳንም ጭምር) ማኅበር እንዲታነጽበት የተሰጡ ሲሆን በልሳኖች መናገር ግን በተጨማሪ ተናጋሪውም የሚታነጽበት ስጦታ ነው።

ያ በሌሎች ልሳናት የተነገረው ነገር በሚታወቅ ቋንቋ ማለትም ተናጋሪው በማያውቀው ሰሚዎቹ ግን በሚያውቁት ቋንቋ ሊሆን ይችላል። በሐዋ.2:4-13 የምናገኘው ይህንን ነው። ይህ በሆነበት በበዓለ ኅምሳ ዕለት በሌሎች ቋንቋዎች የተናገሩት አይሁድ ሲሆኑ የተናገሩበትን ቋንቋ ከቶ አያውቁትም። ሰሚዎቹ ደግሞ ያለ አስተርጓሚ የገዛ ቋንቋቸውን ይሰሙ ነበር።

በሌላ ቦታ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ልሳኖች ሲናገር ተናጋሪውም ሆነ ሰሚዎቹም የማያውቁት ቋንቋ እንዳለም ይናገራል። እንዲህ ያለው ልሳን በጉባዔ በሚነገርበት ጊዜ ተናጋሪውም ሆነ ሰሚዎቹ ለተነገረው ነገር እንግዳ መሆናቸው እርግጥ ነው። ስለዚህ የተነገረው ነገር ሰዎቹ በሚያውቁት ቋንቋ መተርጎምና ሰሚዎቹ (ተናጋሪውም እንደ ሰሚ) በተነገረው ነገር መታነጽ አለባቸው። በልሳናት የተነገረውን መተርጎም ራሱ በልሳናት እንደመናገር ሁሉ ስጦታ ነው። በልሳናት የሚናገር ሰው የተነገረውን እንዲተረጉም እንዲችል ወይም የመተርጎም ስጦታም እንዲኖረው መጸለይ እንዳለበት የተነገረው ለዚህ ነው። ትርጉሙ ተናጋሪው የመተርጎምም ስጦታ ካለው በራሱ በተናጋሪው ወይም በሌላ በልሳናት የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ባለው ሰው ሊተረጎም

ያስፈልገዋል። ካልተተረጎመ ማኅበሩ ሊታነጽበት በምንም መንገድ አይችልም።

ራስን ማነጽ የሚባለው ይህን ስጦታ ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው ባህርይ ተናጋሪው ይህን በሚናገርበት ጊዜ ራሱን እራሱ በሚገባው መንገድ የሚያንጽበትና ሊተረጉመው የማያስፈልገው ነው። ራሱን የሚያንጸውም የመንፈስ ቅዱስን ሕልውና በሕይወቱ በመረዳቱ ነው። ደግሞም በልሳን የሚናገረው ሰው የሚናገረው ለራሱ እንደሆነ ካወቀ እንደማይተረጎምና መተርጎምም እንደሌለበት ከተረዳ ይህን የሚያደርገው በማኅበር ወይም በጉባዔ ከሆነ ድምፁን ማሰማት አይኖርበትም። በልሳናት መናገር ማነጫ ወይም መታነጫ እንጂ ማወኪያ ወይም ልዩ የመሆን መታወቂያ አይደለም። ይህን ከተረዳ ያ ሰው በማኅበር ውስጥ ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር ነው መናገር ያለበት።

በልሳኖች መናገር ዓላማው ላላመኑት ምልክትና እንዲሁም እንደሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ ደግሞ ማኅበረ-ምዕመናንን ማነጽ ነው። በጉባዔ በልሳኖች ከተነገረ ትርጉሙም መጠበቅ አለበት። ትርጉም ካልኖረ ጉባዔው አይታነጽበትምና እንደዚያ መቀጠል የለበትም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እንደ ቃሉ ሁሉ ነገር በስርዓትና በአግባብ መሆኑን ማየት አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ማድረጋቸው የመንፈስ ቅዱስን ስራ መከልከል መስሎ መታየት የለበትም። በእርግጥ መስሎ የሚታይበትም ሆነ የሚሆንበት ሁኔታም ሊኖር ይችላልና ጠንቃቃ መሆን ያሻል። ሚዛኑ ከተጠበቀ ግን ጤናማና ገንቢ እንጂ ጎጂና አፍራሽ አይደለም። በተጨማሪም ስርዓትና አግባብ ብቻ ሳይሆን መናፍስትን የመለየት ስጦታም በስራ መታየት ይጠበቅ ዘንድ ያስፈልጋል ምክንያቱም በልሳኖች መናገር ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ ሁሉ ከአጋንንትም ሆነ በስሜት ከመነዳት እንዲሁም ከሌሎች ብዙ ጊዜ ከመስማት የተነሳም በኩረጃ ሊመጣ ይችላል። ተናጋሪው አንዳንድ ጥያቄዎችን ቢጠየቅ በጥሞና ለመስማትና በትህትና ለመመለስ ፈቃደኛ መሆን አለበት። በልሳኖች የሚናገር አማኝ ስጦታውን የማክበር፥ ፍቅርን የማሳየትና ሌሎችንም ለማነጽ የመትጋት ኃላፊነት አለበት።

በልሳኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ማለት አንድ አማኝ በልሳኖች ሲነገር የተነገረውን ነገር ጉባዔው በሚያውቀው ቋንቋ ለጉባዔው እንዲናገር ለዚያ ሰው የሚሰጠው የመልእክቱ ምንነት መከሰት ወይም መገለጥ ነው። የመተርጎም ስጦታ ቃል በቃል መልዕክቱን የማስተላለፍ የቱርጁማንነት አገልግሎት አይደለም። መልዕክቱ የተነገረበት ቋንቋ የመላእክት ይሁን የሰው፥ ከሰውም የዚህ ይሁን ወይም የዚያ ያ የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ያንን ቋንቋ አያውቀውም። ጉዳዩም ከመልእክቱ እንጂ ከቋንቋው አይደለም። ትርጉሙንም

ያወቀው ቋንቋውን ስላወቀው አይደለም። ምናልባት ቋንቋው የሚታወቅም ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በልሳን የተነገረው መልእክት ካንቶንኛ በሚባለው የቻይና ቋንቋ ቢሆን የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ያን ቋንቋ የሚያውቅ ቢሆን የሚተረጉመው ግን እንደ አስተርጓሚ ሳይሆን እንደ ተርጓሚ ወይም እንደ መልእክት አስተላላፊ በመሆን ነው። የመተርጎም ስጦታውም ልክ እንደ ልሳኑ ሁሉ መለኮታዊ ስጦታ ነው።

በጉባዔ ትርጉም ከሌለ ማኅበሩ መታነጽ አይችልም። ለዚህም ነው ጳውሎስ በጉባዔ ካልተተረጎመ እልፍ (አስር ሺህ) ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮ (ጉባዔው በሚያውቀው ቋንቋ ማለት ነው) መናገር የመረጠው። የማይተረጎም ልሳን በጉባዔ መነገር የለበትም። ትርጉም በሚታወቅ ቋንቋ የሚደረግ በመሆኑ ደግሞ ይህ ስጦታ ከልሳኖችም ይልቅ ተጨማሪ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ተናጋሪው እንዲተረጉም መጸለይ አለበት። የግድ ግን ተርጓሚው እርሱ ብቻ መሆን አለበት ማለት አይደለም። አንድ አማኝ ስጦታው ይህ ከሆነ ለመተርጎም በልሳኖች የሚናገር መሆን የለበትም፥ መናገር ሳይችልም መተርጎም ይችላል። የሚተላለፈው ደግሞ ቃል በቃል በመተርጎም ሳይሆን መልእክቱ ነውና በልሳኖች የተነገረውና የተቱረጎመው የሚወስዱት ጊዜ እኩል ላይሆን ይችላል። ጊዜው የግድ መሳ ለመሳ መሆን የለበትም። አንድ መልእክት በልሳናት ከተነገረ የአምልኮው መሪ ወይም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል አንዱ የሚተረጉም እንዳለና እንዲተረጉም በመጠየቅ ጊዜ መፍቀድ አለበት። በልሳናት እንደመናገርም ሁሉ በሚተረጎምም ጊዜ መናፍስትን የመለየት ስጦታ መኖር አስፈላጊ ነው። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ያላቸው አማኞች በልሳናት የተነገረው ያ መልእክት ከመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ከሌላ ምንጭ መሆኑ ከታወቃቸው ሌላና ተጨማሪ ውዥንብር ስለሚፈጥር መተርጎሙ አስፈላጊ አይሆንም።

በልሳናት መናገርና ትንቢትን መናገር ከሌሎቹ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ይልቅ ሰፋ ያለ ትንታኔ ተሰጥቷቸዋል፤ ይህን በ1ቆሮ.14 እናገኛለን። ይህ ማለት ስጦታን ከስጦታ ለማበላለጥ ሳይሆን የማነጽ ደረጃቸውን ማበላለጡ ነው። መፈለግ ያለበት ይበልጥ የሚያንጸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ትንቢትን መናገር በልሳኖች ከመናገር ይልቅ ጉባዔውን ያንጻልና የቆሮንቶስ ምዕመናን ከልሳኖች ይልቅ ትንቢትን እንዲፈልጉና እንዲናገሩ ያበረታታቸዋል። ትንቢት ከልሳኖች እንደሚሻልና ይበልጥም ጠቀሚታ እንዳለው ሐዋርያው ይህን የተናገረበትን በተለይ በ14: 1፥5 እና 19 እናገኛለን።

በልሳኖች መናገርን በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ ያሰፈራቸው መሠረታዊ መመሪያዎች አሉ እነዚህም፤

ሀ. በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ (:2) (ትንቢት የሚናገር ግን ለሰው ይናገራል።)

ለ. ልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ (:4) (ትንቢት የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።)

ሐ. በልሳን የተነገረ ነገር ካልተተረጎመ ከንቱ ነው፤ (:5-12)

መ. በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ፤ (:13)

ሠ. ለሌሎች ትምህርት ይሆን ዘንድ በልሳን 10 ሺህ ቃላት ከመናገር የሚታወቁ አምስት ቃላት መናገር ይበልጣል፤ (:19)

ረ. በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው፤ (:22) (ትንቢት ግን ለሚያምኑ ምልክት ነው። (በልሳኖች መናገር ለማያምኑ እንዴት ምልክት እንደሚሆን በተለይ በሐዋ.2 ከተጻፈው እንማራለን።)

ሰ. ሁሉ በልሳኖች በሚናገሩበት ያልተማሩ ወይም ያላመኑ ቢገቡ ነገሩ እብደት ሊመስል ይችላል (:23) (ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን ውጤቱ መወቀስና ስግደት ነው።)

ሸ. በልሳን የሚናገሩ ከኖሩ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም፤ (27)

ቀ. የሚተረጉም ከሌለ ግን በማኅበር መካከል ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር፤ (:28)

በ. በልሳኖች መናገር መከልከል የለበትም፤ (:39)

ከላይ የተዘረዘሩት እስከተፈጸሙ ድረስ በልሳኖች መናገር መከልከል የለበትም።

## የሐዋርያነት ስጦታ

"እግዚአብሔርም...አስቀድሞ ሐዋርያት...አድርጎአል።" 1ቆሮ.12:28

"እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት እንዲሆኑ ሰጠ።" ኤፌ.4:11

በአማርኛ ሐዋርያ የሚለው ቃል 'ሐወረ' ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ነው። ትርጉሙም ሄደ የሚለው ግስ ሲሆን ሐዋርያ ማለት 'የሄደ ወይም የተላከ' ማለት ነው። ሐዋርያ የሚለው ቃል የተገለጠበት የግሪክ ቃል ከአዲስ ኪዳን ውጪ ያለው ትርጉሙ አዝማች ወይም የጦር መርከቦች አዛዥ እንደማለት ነው። ይህ ማለት አንድ ተልዕኮን ለመፈጸም የተላከ ባለስልጣን እንደማለት ነው። ይህ ሰው የተላከም ነው ስልጣንም አለው። በአዲስ ኪዳን የምናገኘው ሐዋርያ የሚለው አሳብም ሁለቱንም ማለትም ተልዕኮንና ስልጣንንም የሚያጣምር ነው።

የመጀመሪያዎቹን አስራ ሁለት ሐዋርያት ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የመረጠውና 'ሐዋርያት' ብሎ የሾማቸው ጌታ ራሱ ነው። (ሉቃ.6:13፤ ማቴ.10:1፤ ማር.3:13-15) ከነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው እነዚህን ሐዋርያት፤

- ጌታ ራሱ በፈቃዱ ነው የመረጣቸው

- ለተልዕኮ ነው የመረጣቸው

- ደግሞም ስልጣንም ነበራቸው።

ከነዚህ ከአስራ ሁለቱ አንዱ የሆነው የአስቆሮቱ ይሁዳ ሲሞት በምትኩ ከሐዋርያት ጋር እንዲቆጠር ማትያስ በዕጣ ነበር የተመረጠውና የተሾመው። እኒህ አስራ ሁለቱና ማትያስም ጭምር (ምንም በዕጣም ቢሆን) በጌታ የተመረጡና የተሾሙ ነበሩ። ከነዚህ በኋላ ደግሞ ጥቂት ቆይቶ ሳውል የነበረውን ጳውሎስን ጌታ ሐዋርያ አድርጎ መረጠው ሾመውም። (ሮሜ.1:1፤ 2ቆሮ.12:11-12) የነዚህ ሐዋርያት የሐዋርያነታቸው መመዘኛ ከጌታ ጋር መሆናቸው ወይም ጌታን ማየታቸው ሲሆን ምልክቱም ድንቅና ምልክቶች በእጃቸው መደረጋቸው ነበሩ። እኒህ ልዩ ቦታም ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ቆርቋሪዎች ናቸውና በጌታ ዘንድና በቅድስቲቱም ከተማ ልዩ መታሰቢያ አላቸው። (ኤፌ.2:20 እና ራዕ.21:14) እንዲህ ያሉት ሐዋርያት ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሉም። ስጦታው ወይም ሹመቱ ግን መኖሩን ከ1ቆሮ.12 እና ከኤፌ.4 እናገኛለን።

ይህ ስጦታ ወይም ሹመት ወንጌል ወዳልደረሰባቸውና

ወዳልተሰማባቸው አገሮችና አውራጃዎች በመሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ የምሥራቹን ቃል የማብሰርና የአማኞችን ማኅበሮች የመመስረት ልዩ ስጦታ ነው። በሐዋ.14:14 በርናባስ ከጳውሎስ ጋር ሐዋርያ ተብሎ ተጠርቶ እናገኘዋለን። ይህ በልስጥራን ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን የሰበኩበት ጊዜ ነው። የሐዋርያነት ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን የተዘራው የቃሉ ዘር እንዲያድግና እንዲያፈራም በመታገስ የሚጋደሉ አገልጋዮች ናቸው። ጳውሎስንና በርናባስን የሾመቻቸው ወይም የላከቻቸው የአንጾኪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ይህንንም ያደረገችው በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት ነበር። (ሐዋ.13) የላከቻቸው የወንጌል መልእክተኞች ማለትም እንደ ሁለተኛው የቃሉ ትርጉም ሐዋርያት አድርጋ ነው። በዚህም ምክንያት ጳውሎስን ስንወስደው በጌታ ጥሪም በስጦታም ሐዋርያ ነው ማለት ነው።

ይህ የሐዋርያነት ስጦታ እንደዚህኛው ባለው መንገድ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ቤተ ክርስቲያን የወንጌልን መልእክት አስይዛ የምትልካቸው ሰዎች በዚህ ስም ሊጠሩ ይቻላቸዋል። እነዚህ ሰዎች ጥልቅ ሸክማቸው ወንጌል ባልተሰበከበት የክርስቶስን ወንጌል መናገርና አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ነው። እነዚህ ይህን እንዲያደርጉና ሲያደርጉም ቤተ ክርስቲያን እንድታውቅና እንድትደግፍም ይጠበቅባታል።

## የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ

"ሌሎቹም ወንጌል ሰባኪዎች እንዲሆኑ...ሰጠ።" ኤፌ.4:11 ወንጌልን የመስበክ ስጦታና ወንጌልን የመናገር ኃላፊነት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ወንጌልን መናገር ወይም መመስከር ማለትም ደኅንነት በክርስቶስ ብቻ የመገኘቱን እውነት ላልዳኑ መናገር የማንኛውም ክርስቲያን ኃላፊነት ነው። ሁሉም ክርስቲያን የመመስከር ኃላፊነት አለበት ማለት ግን አማኝ ሁሉ የወንጌል ሰባኪ ነው ማለት አይደለም። ሁሉ መስጠት ቢኖርባቸውም ጥቂቶች ግን የመስጠት ልዩ ስጦታ እንዳላቸው ወይም ሁሉ የመማር ማለትም የርኅራኄ ኃላፊነት ቢኖርባቸውም ጥቂቶች ደግሞ ይህ ስጦታ እንዳላቸው አሁንም ሁሉም ወንጌልን የመናገር ኃላፊነትና የፍቅር ግዴታ ኖሮባቸው ጥቂቶች ግን ስጦታው አላቸው።

በኤፌ.4:11 የተጻፈው የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ (ወይም ሹመት) ወንጌላዊ የሚለው ቃል ነው። ይህ ቃል ከዚህ ቦታ ሌላ በሁለት ቦታዎች ብቻ ይገኛል፤ እነዚህም ፊሊጶስ ወንጌላዊ መሆኑ የተገለጠበት ሐዋ.21:8 እና በ2ጢሞ.4:5 ጢሞቴዎስ የወንጌል ሰባኪነትን (ማለትም የወንጌላዊነትን) ሥራ

እንዲፈጽም የተነገረበት ስፍራ ናቸው። ስጦታው እንደ ጸጋ ስጦታ ለአማኙ የተሰጠ ሲሆን ያ አማኝ ደግሞ እንደ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ አገልጋይ ነው። ቤተ ክርስቲያንም ስጦታውንና ስጦታነቱንም በተመለከተ በመስኩ እንዲሰማራ ልትጠራው ወይም ልትሾመው ይገባታል።

ይህ የጸጋ ስጦታ ያለው ሰው ላልዳኑ ሰዎች የወንጌሉን መልእክት የማድረስ ሸክም ብቻ ሳይሆን ልዩ ችሎታና ድፍረትም አለው። ሰዎቹም ሊገባቸው በሚችል ግልጽና ቀላል ቋንቋ መልእክቱን ማስተላለፍ ይችላል። ይህ አገልግሎት እንደ ተልዕኳዊ ወይም ሐዋርያዊ አገልግሎት በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ከአገልግሎቱ ባህርይ እንደምንረዳው እነዚህ ይህ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ጊዜያቸውን በሙሉ ሰጥተው የሚያገለግሉ ከሆነ የሚያደርጉት ነገር ወንጌልን በአንድ ቦታ ሰብከው የመመገቡንና የማሳደጉን ኃላፊነት ለሌላው በመስጠትና በመተው ወደ ሌላ ወንጌል ወዳልተነገረበት በመሻገር ማገልገል ነው። ይህ የወንጌል ስብከት ስጦታ ያለው ሰው የማስተማሩም ስጦታ አብሮ ከኖረው በማስተማርና በማሳደግ መቆየትም ኃላፊነቱ ይሆናል። ጳውሎስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ጳውሎስ የወንጌል ሰባኪም ጥሩ አሳዳጊም ነው።

የጳውሎስን የወንጌል ስብከት ስጦታ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ እናየዋለን። ጳውሎስ ሸክሙም ሆነ ስጦታውም ነበረው። ስልቱን ደግሞ እንደሚያገኛቸው ሰዎች ዓይነት ይለዋውጥ ነበር። ለምሳሌ፤

- የጲስድያ በትምህነው አንጾኪያ ለአይሁድ፤ (ሐዋ.13:13-43)

- በልስጥራን ለሚገኙ ለአረማውያን፤ (ሐዋ.14:8-18)

- በአቴና በአርዮስፋጎስ ለነበሩት፤ (ሐዋ.17:22-34)

እነዚህን ሦስት ቦታዎች ስንመረምር የነበሩትም ሦስት ዓይነት ሰዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ጳውሎስ ለሁሉም ያቀረበው ያው አንዱን ወንጌል ቢሆንም እንደየሰዎቹ ልዩነት የአቀራረቡ ስልትና የማስረጃ ነጥቦቹ የተለያዩ ነበሩ። ለአረማውያኑ ዳዊትን አልነገራቸውም ወይም ለአይሁድ የግሪክን ባለ ቅኔ አልጠቀሰም። ጳውሎስ የወንጌል ሰባኪነት ብቻ ሳይሆን ከዚያ የሚቀጥለውም አገልግሎት ሸክም እንደነበረውም ከሐዋ.15:36 እንረዳለን።

አማኞች ሁሉ በሚችሉት መንገድና በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወንጌልን የማዳረስ ኃላፊነት ቢኖርባቸውም በእግዚአብሔር መለኮታዊ አሰጣጥ ደግሞ

የተወሰኑት የወንጌል መስበክ ልዩ ስጦታ ወይም የወንጌላዊነት አገልግሎት አላቸው። አማኞች ይህን ድንቅ አገልግሎት በነዚህ ሰዎች ትከሻ ብቻ በመጣል ነፃ የመሆን አዝማሚያ ሊታይብን አይገባም። የእነዚህን ወገኖች ስጦታ በማወቅ ለእነርሱ ሕይወትና ለወንጌሉም መሮጥ መጸለይና በሚቻለው ሁሉ ደግሞ ለአገልግሎታቸው መሳካት መተባበር አስፈላጊና የሚጠበቅም ነው።

## የእረኝነት ስጦታ

"ሌሎቹም እረኞችና...እንዲሆኑ ሰጠ።" (ኤፌ.4:11)

የእረኝነትን ስጦታ የምናገኘው በኤፌ.4 ነው። በኤፌ.4:11 የተዘረዘሩት አራት ወይም አምስት ስጦታዎች እንደ ስጦታ ብቻ ሳይሆን እንደ ሹመትም የሚታዩ መሆናቸውን ተመልክተናል። እግዚአብሔር አንዳንዶችን እረኞች (ወይም እረኞችና አስተማሪዎች) አድርጎ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት "እረኞችና አስተማሪዎች" የሚለውን ሐረግ እንደተጣበቀና አንድ ድርብ ስጦታ እንደሆነ አድርገው ያስተምራሉ። ይህ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ቢሆንም ግን ማስተማርን አስቀድመን ስላየን እዚህ ላይ እረኝነትን ብቻ እናያለን።

በኤፌ.4 የተዘረዘሩት ስጦታዎች ወይም ሹመቶች አካሉን የማነጽ አገልግሎቶች እንደመሆናቸው እረኝነትም ተመሳሳይ ግብ አለው። ስለዚህ የእረኛ የስጦታው ግብ መቀለብ ብቻ ሳይሆን አንዱ አማኝ ሌላውን መመገብና ማነጽ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸትም መሆን አለበት። ይህ የሩቅ ግቡ ነው ማለት ነው።

የወንጌል ሰባኪነትና የሐዋርያነት አገልግሎቶች በአንድ ቦታ ወንጌልን በመስበክ ሰዎችን ከክርስቶስ ጋር በማስተዋወቅ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ሲሆን የእረኝነትና የማስተማር አገልግሎት ግን ከዚህ በኋላ ያለውን አገልግሎት ተረክቦ የመቀጠል ኃላፊነት ነው። የማስተማርና የእረኝነት አገልግሎቶች በጣም የተቀራረቡ ናቸው ለዚህም ይሆናል እረኞችና አስተማሪዎች የሚለውን ቃል አንዳንዶች የሚያጣብቁት። እረኝነት የሚለው የአዲስ ኪዳን የግሪክ ቃል 'ፓስተር' የምንለው ቃል የተሰራበት ነው። ጌታችን ራሱን በዚህ ቃል ጠርቷል (ዮሐ.10) ለስምዖን ጴጥሮስ ይህን ኃላፊነት ሰጥቶታል (ዮሐ.21) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም በዚህ ስም ተጠርተዋል።

(ሐዋ.20) የቃሉ ጥሬ ትርጉም መንጋን መጠበቅ፥ ማሰማራት፥ መመገብ፥ መከባከብ፥ መመሰግ ማለት ነው። በአጠቃላይ አጋጅ ወይም እረኛ ማለት ነው።

ይህ የእረኝነት ስጦታ እንግዲህ ልክ እረኛ ለከብቶቹ የሚያደርገውን ነገር ለምዕመናን የማድረግ ኃላፊነትን የመወጣት ስጦታ ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከጠላት መከላከልን፥ ጥሩ አድርጎ መመገብን፥ ከመንገድ ሲስቱ መመለስንና ማቅናትን፥ ሲጠፉ መፈለግን፥ ሲጎዱና ሲሰበሩ ማከምንና መጠገንን ሁሉ ያካትታል። እረኛ ከመንጋው መራቅ እንደሌለበት ይህኛውም ከምዕመናኑ በማናቸውም ነገር ሳይርቅ ነው ማገልገል ያለበት። አብሮ መውጣትና መውረድም ያለበት አገልግሎት እንደመሆኑ ከማስተማር አገልግሎት ይልቅ ለምዕመናኑ ሕይወትና የየዕለት ኑሮ የቀረበና ራስን የማመሳለስንም ዋጋ የሚጠይቅ ነው። አገልግሎቱ ምንም ያህል ዋጋ ቢጠይቅ ስጦታው ያለው አገልጋይ ሰማያዊው ችሎታ ስላለው ለማገልገል አይታክትም። ምዕመናንም እርሱን መሳይ እረኞች ጌታ እንዲሰጠን በመጸለይ ለእነዚህም አገልጋዮች ምቹ መሆን ሲጠበቅብን እረኞች ደግሞ ይህን ከባድ ዋጋ በጌታ ጸጋ ለመክፈልና ለማገልገል መፍቀድ አለባቸው።

## የጸጋ ስጦታን ማወቅ

የጸጋ ስጦታ እንዴት ይታወቃል? አንድ ክርስቲያን ፍሬያማ አገልግሎት ይኖረው ዘንድ ይህን ጥያቄ መመለስ መቻል በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ያለዚያ ያልሆነውን ለመሆን ያልተሰጠውን ለመስጠት ሲታገል የሆነውን ሳይሆን ያልሆነውንም ለመሆን ሲሞክር ውድ ዘመኑን ይፈጃል። የጸጋ ስጦታን ማወቅ ሚዛን ላይ ወጥተን ቁመን ክብደታችንን እንደምናውቀው ወይም ጠብታ ደም ሰጥተን የደማችን ዓይነት እንደሚነገረን ወዲያው የሚሆን ነገር አይደለም። የጸጋ ስጦታ በጊዜና በሂደት ውስጥ የሚታወቅ ነገር ነው። ብቻችንንም የምናውቀው ሳይሆን ሌሎች አማኞችም ከአገልግሎታችንም ሆነ ከመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የተነሳ የሚያዩትና የሚያረጋግጡልን ነገር ነው።

የጸጋ ስጦታችንን ለማወቅ ጥቂት መሠረታዊ ነገሮችን ማወቅ ያስፈልገናል። ከእነዚህም ጥቂቶቹና ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉት የሚከተሉት ናቸው።

1. ስጦታዎችን በተመለከተ ሊኖረን የሚገባው ግንዛቤ በቂና ጤናማ መሆን አለበት። ይህ ማለት የጸጋ ስጦታዎች ምን መሆናቸውን፥ እነማን

መሆናቸውን፥ ከተፈጥሮ ችሎታዎችና ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚለዩት በምን እንደሆነ ከቅዱስ ቃሉ ማወቅ ነው።

2. ከስጦታዎች በጥቂቶቹ ወይም በሁሉም በጥልቀትም ባይሆን ለመሳተፍና ለማገልገል መሞከር። በስጦታዎቹ ለማገልገል ሙከራ ስናደርግ በሌሎች ሁኔታዎች ላለመገፋትና በስሜት ባለመወሰድ ቢሆን በውስጣችን ያለውን ስጦታ በእርግጠኛነት እንድናውቀው ሊያደርገን ይችላል።

3. የቤተ ክርስቲያንን ማለትም የሌሎችን አማኞች ማረጋገጫ በማስተዋል መስማት። አንዳንዴ ስጦታ ያለን እየመሰለን ወይም ስሜታችን እየነገረን ሌሎች እንደሌለን የሚያረጋግጡልን ወይም ደግሞ የሌለን እየመሰለን ሌሎች እንዳለን የሚነግሩን ጊዜ ይኖራል። የሰውነታችንን አካላዊ ቅንብር ስናስተውል የአንዱን ብልት ሥራ ሌላው ያውቃል ያረጋግጣል ይቀበላልም። እንደዚሁም ሁሉ ሌላው የክርስቶስ አካል ማለትም የቤተ ክርስቲያን ብልት የሆነ አማኝ የኛን ምን ዓይነት ብልት መሆን ሊያረጋግጥልን እንደሚችልም መሳት የለብንም።

4. ውጤታማ ወይም ፍሬያማ አገልግሎት ሊኖረን ይገባል። በተሰጠን ስጦታ ወይም በተሰማራንበት አገልግሎት ስንውል የምናመርተው ፍሬና ውጤታማነታችን በስጦታችን የመሰማራታችንም ምልክት ሊሆን ይችላል። የጸጋ ስጦታ ዋና ፍሬ ወይም ዓላማ ሌላ ሳይሆን የክርስቶስ አካል ማለትም የማኅበረ ምዕመናን መታነጽ ነው። በስጦታችን ስንሰማራ ይህ እየሆነ ነው? ውጤት ሲባል ቶሎ የሚታይም የማይታይም ሊሆን ይችላል። ደግሞም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሌሎችም የራስም ጤናማ ምስክርነት አጥብቆ ሊታይ ያስፈልጋል።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቂት የስጦታ ማወቂያ ነጥቦች በቅንነትና በጸሎት በመደገፍ ተግባራዊ ማድረግ መንፈስ ቅዱስ በኛ ውስጥ ያኖረውን ስጦታ ወይም ስጦታዎች ለማወቅ ሊረዳን ይችላል። ከዚህም ሌላ በአንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች አማካይነት የተዘጋጁ የስጦታ መለያ ወይም ጠቋሚ መጠይቆች አሉ። እነዚህ መጠይቆች የስጦታ ማረጋገጫ እንጂ ማግኛ አይደሉም። ደግሞም ከመጠን ያለፈና የተለየ ትኩረትም ሊሰጣቸው አይገባም።

ከዚህ በታች አንድ የስጦታ ጠቋሚ ሊሆን የሚችል መጠይቅ ይገኛል። ይህ መጠይቅ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አገልጋዮች ያዘጋጁቸው ሲሆኑ ይህ ከታች የሚገኘው ዝርዝር ከነዚህ የተለያዩ ምንጮች የተውጣጣ ነው። ቀደም ሲል በዝርዝር ከተመለከትናቸው አስራ ስምንት የጸጋ ስጦታዎች በተጨማሪ ሁለት ተጨምረው ሃያ ሆነዋል። መጠይቁ በግል ወይም በቡድን ሊሰራበት የሚችል ሲሆን አሰራሩ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው።

ሀ. ጠቋሚ መጠይቁ ሦስት ክፍሎች እንዳሉት አስተውል፤

ለ. ወደ ክፍል አንድ በመሄድ በማስተዋል ካነበብክ በኋላ ረጅም ጊዜ ሳይቆይ በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ በስተቀኝ ካሉት ሳጥኖች ውስጥ የ"x" ምልክት አድርግ። በአንድ ጊዜ አንዱን መጠይቅ ብቻ ተመልከት።

ሐ. ከዚያም ወደ ክፍል ሁለት በመሄድ በክፍል አንድ የተሞሉትን ውጤቶች በየቁጥሮቹ አጠገብ በየሳጥኑ ውስጥ አስቀምጥ። የውጤቶቹ ቁጥር ከ0 እስከ 3 ይሆናል።

መ. ቀጥሎ የአግድመት ድምራቸውን ውጤት "ጠቅላላ" ከሚለው በታች ጻፍና ወደ ክፍል ሦስት በመሄድ የመጨረሻውን ክፍል ሙላ።

# ክፍል አንድ

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማስተዳደር ስራዎችን ማለት ማቀድ፣ ማደራጀት፣ ኃላፊነት መስጠት ወዘተ. ለመስራትም ሆነ ለመማር ፈቃደኛ ነኝ። | | | | |
| 2 | ቤተ ክርስቲያኔ የጠፉትን ለመድረስ ወንጌላውያንን ለመላክ በምታደርገው ጥረት ደስተኛና ተባባሪም ነኝ። | | | | |
| 3 | አንዳንድ ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የሚጋጩ የሚመስሉኝ ጊዜዎች አሉ። | | | | |
| 4 | የተረዳሁትን ያህል የወንጌሉን መልእክት ማካፈል ያስደስተኛል። | | | | |
| 5 | የኑሮ ችግር ወይም ቀውስ የገጠማቸውን ሰዎች ተቀብዬ እረዳለሁ። | | | | |
| 6 | እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ ጥብቅ የሆነ እርግጠኛነት አለኝ። | | | | |
| 7 | ሰዎች ፈጣን የሆነ የገንዘብ እርዳታ ፈልገው ሲቸገሩ በቶሎ የዕርዳታ ምላሽ እሰጣለሁ። | | | | |
| 8 | በቤቱ ውስጥ ማገልገል የሚፈልጉ ሰዎችን በማስተናገድ ከፍተኛ እርካታን አገኛለሁ። | | | | |
| 9 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን የማንበብ፣ የማጥናትና የመማር ኃላፊነት እንዳለብኝ ይሰማኛል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ሌሎችን ሰዎች ለአንድ የሆነ አገል ግሎት መስክ ማንሳሳትን ቀላል ሆኖ አገኘዋለሁ። | | | | |
| 11 | ስለሌሎች ማለትም በድኅነት ለተመቱ፥ በበሽታ ለተጎዱ፥ እንግዶችና ባይተዋሮች ለሆኑና ለታሠሩ ሰዎች አብሬአችው እንደተጎዳሁ ያህል ይሰማኛል። | | | | |
| 12 | ሌሎች አማኞችን የሚገነቡ፥ የሚ ያበረታቱና የሚያጽናኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን የመግለጥ ኃላፊነት ይሰማኛል። | | | | |
| 13 | የሌጋ ክርስቲያኖችን መንፈሳዊ ሕይወት ለመጠበቅ ራሴን ልሰጥ ተዘጋጅቻለሁ። | | | | |
| 14 | ሰዎችን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ለመርዳት ዝግጁነት ይሰማኛል። | | | | |
| 15 | የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ሰዎች በትክክል መረዳትና ከሕይወታቸውም ጋር ማገናዘብ እንዳለባቸው ጠንካራ እምነት አለኝ። | | | | |
| 16 | ለእግዚአብሔርና እርሱም ለኔ ሕይወት ስላለው ፈቃድ አክብሮት አለኝ። | | | | |
| 17 | የምሥራቹን ቃል በማላውቀው ቋንቋ እንድናገር እግዚአብሔር ረድቶኛል። | | | | |
| 18 | በጸሎቴ ምክንያት እግዚአብሔር አንድ የማይቻል ነገር አከናውኗል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 19 | በጸሎቴ አማካይነት ሰዎች ሲፈወሱ አይቻለሁ። | | | | |
| 20 | አንድ መልእክት በልሳኖች ሲነገር ትርጉሙ በውስጤ ይታወቀኛል። | | | | |
| 21 | ቤተ ክርስቲያን የምታቅደውን የሆነ ፕሮግራም ፍሬያማነት ውጤቱን በማጥናትና በመገምገም መረዳት እችላለሁ። | | | | |
| 22 | ሌላ ባህልና ቋንቋ ያላቸውን ሰዎች ለማገልገል በሚደረገው ሙከራ አነስተኛነት አዝናለሁ። | | | | |
| 23 | መንፈሣዊ እውነት ያልሆኑ ነገሮችን ከተፈጥሮ ውጪ ከሆኑ መገለጦች መለየት እንደምችል አንዳንድ የበሰሉ ክርስቲያኖች ይነግሩኛል። | | | | |
| 24 | እምነቴን ለማካፈል እንድችል ክርስቲያን ካልሆኑት ጋር ግንኙነት መፍጠር እሻለሁ። | | | | |
| 25 | ለሚሰቃዩና አዕምሮአቸው ለታመሙ ሰዎች የጠለቀ የኃዘኔታ ስሜት ይሰማኛል። | | | | |
| 26 | በአንዳንድ የጸሎት ርዕሶች ላይ ሳላቋርጥ በመጸለዩ እደሰታለሁ። | | | | |
| 27 | የእግዚአብሔርን ሥራ ለመርዳት ዝቅተኛ በሆነ ኑሮ ለመኖርም ፈቃደኛ ነኝ። | | | | |
| 28 | ቤቴ ያን ያህል የጸዳና የተመቻቸም ባይሆን ለሌሎች በሬን በመክፈት ደስታ ይሰማኛል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 29 | በቆላ.1:10 ላይ ጳውሎስ "በእግዚአብሔርም ዕውቀት እያደጋችሁ" ያለው ቃል አጥብቄ የምቀበለው ነው። | | | | |
| 30 | የተወሰኑ ሰዎችን በቡድን አስተባብሮ የጋራ ግባቸውን እንዲመቱ መምራት ያስደስተኛል። | | | | |
| 31 | ውለታን ለመመለስ ለማይችሉ ወይም ለማይፈልጉ ሰዎች የፍቅርና የበጎነትን ነገር ለማድረግ ምኞቴ ነው። | | | | |
| 32 | መዝሙርን፥ ትምህርትን ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን በማካፈል አማኞች እንዲማሩት ማድረግ ደስ ይለኛል። | | | | |
| 33 | ደቀ መዛሙርትን መርጦ እንዳቸው ሌላቸውን ማገልገል እንዲችሉ የማሰልጠን አስፈላጊነት ይሰማኛል። | | | | |
| 34 | የሚታይ ነገር አድራጊ ከመሆን ይልቅ ከሚደረገው ነገር ጀርባ ሆኜ መርዳትን እመርጣለሁ። | | | | |
| 35 | በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላትን ትርጉም ማወቅ ያስደስተኛል። | | | | |
| 36 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን በመጠቀም ችግሮችን በማያወላዳ መንገድ እፈታለሁ። | | | | |
| 37 | በጸሎት ጊዜ በልሳን ስናገር ልዩ ትርጉም ይሰጠኛል። ሌሎቹም አይታወኩም። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 38 | ሰው ሊያደርጋቸው የማይችላቸውን ነገሮች እግዚአብሔር አከናው ኖልኛል። | | | | |
| 39 | የአካልና የኅሊና ሕመም ያለባቸውን ሰዎች እግዚአብሔር ይፈውሳቸው ዘንድ መጸለይ ደስ ይለኛል። | | | | |
| 40 | በልሳን የተነገሩ መልእክቶችን መተርጎሚ ትክክለኛ መሆኑን በተለያዩ መንገዶች አረጋግጫለሁ። | | | | |
| 41 | አሳቦችን፥ ሰዎችን፥ ነገሮችንና ጊዜን በማስተባበር ፍሬያማ አገልግሎት መስጠት ይቻለኛል። | | | | |
| 42 | አዲስ አጥቢያ ቤት ክርስቲያን በመ ጀመር በኩል ለመተባበር አሳብ አለኝ። | | | | |
| 43 | በሰይጣናዊ ተፅዕኖ እና በአዕምሮ በሽታ መካከል ያለውን ልዩነት ማስተዋል እችላለሁ። | | | | |
| 44 | ክርስቶስ እንዴት አዳኜና ጌታዬ እን ደሆነ ለመናገር ሁሌም ይመቸኛል። | | | | |
| 45 | የኔን ማበረታቻ ተግሳጽም ሆነ ወይም ምክር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሲጠራኝ አብሬው ልሆን ደስተኛ ነኝ። | | | | |
| 46 | የእግዚአብሔርን ምሪትና መንገዶ ቹንም በመፈለግ በእርሱ በጣም እደገፋለሁ። | | | | |
| 47 | ያሉኝ ነገሮችም ሆኑ እኔም እራሴ ብሆን ለእግዚአብሔር አገልግሎት መጠቀሚያ እንደሆንን እቆጥራለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 48 | ቤቴን፣ ዕቃዎቼንም ሆነ ንብረቴን ከቤተሰቤ ውጪ የሆኑ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ፈቃደኛ ነኝ። | | | | |
| 49 | ቃሉን በትክክል ተረድቼ ሳላፍር ለማስተላለፍ እንድችል ለመማር ጥልቅ ጉጉት አለኝ። | | | | |
| 50 | ሕጋዊ መሪዎች ባልተመደቡባቸው ሁኔታዎችና ጊዜያት ኃላፊነት ተሰምቶኝ እመራለሁ፤ ተቀባይነትም አለኝ። | | | | |
| 51 | ችግረኞችንና የጎደሉ ነገሮች ያሏቸውን ሰዎች በመርዳት እረካለሁ። | | | | |
| 52 | የጉባኤ ስብከት መጽሐፍ ቅዱስን የሚገልጥና ከሕይወት ጋር የሚዛመድ ቢሆን እመርጣለሁ። | | | | |
| 53 | አንድ የክርስቲያኖች ቡድን እንዲያድግ ኃላፊነት መቀበል ደስ ይለኛል። | | | | |
| 54 | በተሰጥዖዎቼ ሁሉ ሌሎችን በኃላፊነት ላይ የሚገኙት እንዲጠቀሙበት በማድረግ ደስ እሰኛለሁ። | | | | |
| 55 | ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት የማስተማር-መማር ሂደት አስፈላጊ መሆኑ በጣም ይሰማኛል። | | | | |
| 56 | ሌሎች ሰዎች በስራ ላይ ሊውሉ ስለሚችሉ አሳቦች ወይም ሌሎች አማራጮች ምክር ይጠይቁኛል። | | | | |
| 57 | በጸሎትና በአምልኮ ጊዜ በመንፈስ እሆንና በልሳኖች እናገራለሁ በዚህም ራሴም ሰዎችም ይታነጻሉ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 58 | እግዚአብሔር ጸሎቱን በመባረኩ ብዙ አስቸጋሪና ውስብስብ ነገሮች ወደ መልካም ተለውጠዋል። | | | | |
| 59 | ሕመም ላለባቸው ሰዎች እንድጸል ይላቸው እግዚአብሔር ደጋግሞ ያሳስበኛል። | | | | |
| 60 | በልሳን የሚነገሩ መልእክቶች እንዲ ተረጎሙ እጸልያለሁ። | | | | |
| 61 | ኮሚቴን ወይም አንድን ቡድን የጋራ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ መምራት እችላለሁ። | | | | |
| 62 | በሌላ ኖሬበት በማላውቀው ባህል ውስጥ ሆኜ ለማገልገል እፈልጋለሁ። | | | | |
| 63 | ለመለየት አስቸጋሪ እንኳ ቢሆኑ በእውነትና በስህተት መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ እችላለሁ። | | | | |
| 64 | ከክርስቶስ ጋር ያለኝን የግል ግንኙ ነት ለሌሎች ለመናገር አሳብ አለኝ። | | | | |
| 65 | ልባቸው ለተሰበረና በሱስ ለተጠመዱ ሰዎች ጥልቅ የኀዘኔታ ስሜት ይሰማኛል። | | | | |
| 66 | ለሌሎች ሰዎች ብዙ ከሚጸልዩ ወገኖች ጋር ስሆን ምቾት ይሰማኛል። | | | | |
| 67 | የምሰጠው ገንዘብ በተቻለ መጠን በተገቢ መንገድ ለጌታ ስራ እንዲውል አስባለሁ። | | | | |
| 68 | መጠለያና ፈውስ የሚፈልጉ ሰዎች ቤቱን እንዲጠቀሙበት በተከፈተ ልብ እቀበላለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 69 | የማገኛቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ከሌሎች ጋር ለመካፈል እናፍቃለሁ። | | | | |
| 70 | ሌሎች ሰዎችን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ለመምራትና ለማሳመን ፈቃደኛ ነኝ። | | | | |
| 71 | ሆስፒታል፥ እስር ቤትና የመሳሰሉትን ቦታዎች ለመጎብኘት ፈቃደኛና በዚህም አገልግሎት ደስተኛ ነኝ። | | | | |
| 72 | በዓለማዊ ስርዓት ለሚደረጉ ክፋቶች ለምሳሌ መንግሥት ስለሚያደርጋቸው ስህተቶች ለመናገር አልፈራም። | | | | |
| 73 | አብረውኝ ያሉ አማኞችን የክርስቲያን ተቃዋሚ እንዲሆኑ ከሚያነሳሷቸው ሰዎች የመጠበቅ ኃላፊነት ይሰማኛል። | | | | |
| 74 | የተናቁ ሥራዎችን ወይም በሌሎች ሰዎች እንደ ጠቃሚ የማይቆጠሩ ስራዎችን መሥራት ያረካኛል። | | | | |
| 75 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ከሕይወት ጋር የማዛመድ አስፈላጊነት ያሳስበኛል። | | | | |
| 76 | የእርስ በርስ ግንኙነቶች ሰላማዊ ቅም ነገርን ያዘሉ እንዲሁም ወገናዊና ግብዝ ያልሆኑ እንዲሆኑ በጣም እጥራለሁ። | | | | |
| 77 | ለሰሙት ሁሉ በረከትን ያመጣ መልእክትን በማላውቀው ቋንቋ ተናግሬ አውቃለሁ። | | | | |
| 78 | ለመንግሥቱ መስፋት ምክንያት ተአምራት እንዳደርግ እግዚአብሔር ይጠቀምብኛል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 79 | የአካል ሕመም ስላለባቸው ሰዎች እንድጸልይ ብዙ ጊዜ እጋበዛለሁ። | | | | |
| 80 | በልሳን የተነገሩ መልእክቶች ከናሩና ካልተተረጎሙ መልእክት ካለኝ እንድናገር ተጠይቄ አውቃለሁ። | | | | |
| 81 | ክርስቲያኖች ጥንካሬያቸውን ወይም ስጦታቸውን በአገልግሎት እንዲያሳዩ ላስጀምራቸውና ላነሳሳቸው ይቻለኛል። | | | | |
| 82 | ባልተለመደ ሁኔታ ውስጥ ነፍሳትን መማረክ ያስደስተኛል ደግሞም ይቀልለኛል። | | | | |
| 83 | ብቁ ባልሆነ ነገር ግን ሰዎች በሚቀበሉት ወይም በክፉና በመልካም መካከል ያለ ችግር መለየት እችላለሁ። | | | | |
| 84 | የማያምኑ ክርስቶስን እንዲቀበሉ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ በመሆን መረብ የመጎተት አገልግሎት ማከናወን ያስደስተኛል። | | | | |
| 85 | ደካማውን የሚፍገመገመውንና የተጨነቀውን በቃል እደገፋለሁ። | | | | |
| 86 | የማይቻል በሚመስል ላይ በእግዚአብሔር ኀልውናና ኃይል እታመናለሁ። | | | | |
| 87 | የእግዚአብሔር ሥራ ይሰፋና ይደገፍ ዘንድ በደስታ እለግሳለሁ። | | | | |
| 88 | የዕርዳታ ወይም የመፈወስ አገልግሎት የሚያስፈልገውን ሰው ወደ ቤተሰቤ መጨመር ደስ ያሰኘኛል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 89 | የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች በቀላሉ እረዳለሁ። | | | | |
| 90 | ሁልጊዜ ወደት እንደምሄድ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክርስቲያኖች በዚህ አቅጣጫ እንዲሄዱ ተፅዕኖ ማድረግ እችላለሁ። | | | | |
| 91 | በብዙዎች ዘንድ ችል ከሚባሉ ሰዎች ጋር በደስተኛነት እሰራለሁ። | | | | |
| 92 | ስለ እግዚአብሔር በመግለጥ ብዙ ሰዎችን ማስተማርና ማስጠንቀቅ የአገልግሎቴ ባህርይ ነው። | | | | |
| 93 | የምመራቸውንና የማገለግላቸውን ሰዎች ማወቅና በእነርሱም መታወቅ ለእኔ አስፈላጊ ነገር ነው። | | | | |
| 94 | ሰነዶችን ማስተካከል፣ መተየብ፣ ቃለ ጉባዔዎችን መያዝና የመሳሰሉትን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ስራዎች በመስራት ማገልገል ያስደስተኛል። | | | | |
| 95 | ለአድማጮች የእግዚአብሔርን ቃል ቀጥተኛ ትርጉም ለመግለጥ ጥርት ባለ ሁኔታ የማስተማር ተሰጥዖ አለኝ። | | | | |
| 96 | የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች በተገቢው መንገድ ከሕይወቴ ጋር አጣምዳለሁ። | | | | |
| 97 | እኔ በማላውቀው ቋንቋ የተናገርኩትን ነገር መልእክት ሌላ ሰው ነግሮኝ ያውቃል። | | | | |
| 98 | የሰው አቅም ብቻውን ሊያከናውናቸው የማይችላቸውን ትልልቅ ዕቅዶች እንዳቅድ እግዚአብሔር ደጋግሞ ያሳስበኛል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 99 | በሕመም የሚሰቃዩ ክርስቲያኖች እንድ ጸልይላቸው ይጠይቁኛል። | | | | |
| 100 | አንድ ነገር በጉባዔ ውስጥ በማይታወቅ ቋንቋ ተነግሮ በዚያው በተናጋሪው ወይም በሌላ ቢተረጎም ትርጉሙ ትክክል መሆን ያለመሆኑ ይታወቀኛል። | | | | |
| 101 | ኃላፊነትን ለሌሎች በመስጠት ረገድ ብቁ ነኝ። | | | | |
| 102 | ወንጌልን ለመስበክ፣ ቃሉን ለማገልገል ወይም እንዲህ ያሉትን አገልጋዮች ለመርዳት የኔ ባልሆነ ባህል ተገኝቼ ራሴን ማስለመድ እችላለሁ። | | | | |
| 103 | ሰዎች ቃሉን ሲተረጉሙ የሚሳሳቱትን ስህተት መለየት የመቻል ተሰጥዖ አለኝ። | | | | |
| 104 | ክርስቶስ ያደረገልኝን ነገር በደስታ ለሌሎች እናገራለሁ። | | | | |
| 105 | የመንፈሣዊ ነገር ጥላቻ ያለውን ሰው በቃል መከራከር እችላለሁ። | | | | |
| 106 | እግዚአብሔር በየዕለቱ ጉዳዮቼ ውስጥ ጣልቃ እንደሚገባና እንደሚሳተፍ አምናለሁ። | | | | |
| 107 | እግዚአብሔርን ስለምወደው ገንዘብንና ነገሮችን በነፃና በደስታ እሰጣለሁ። | | | | |
| 108 | አንግዶች ባይተዋርነት እንዳይሰማቸው የማድረግ ችሎታ አለኝ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 109 | የቃሉን እውነትና በውስጣቸው ያሉትን መመሪያዎች ማግኘትም መረዳትም አይከብደኝም። | | | | |
| 110 | ክርስቲያናዊ ባሕሪዬ፥ አኗኗሬና ጠባዬ በአጠቃላይ ሌሎች እኔን እንዲመስሉ የሚያነሳሳቸው ነው። | | | | |
| 111 | ሆስፒታሎችንና የመጠሪያ ቤቶችን መጎብኘት እንዲሁም ለሌሎች የበረከት ምክንያት መሆን ያስደስተኛል። | | | | |
| 112 | የእግዚአብሔርን እውነቶች ግልጽና አሳማኝ በሆነ መንገድ ብዙ ሕዝብ ባለበት እናገራለሁ። | | | | |
| 113 | አዲስ ለሆኑና ከመስመር ለሚወጡ ክርስቲያኖች የጊዜ፥ የገንዘብና የሌሎችን መስዋዕትነት እከፍላለሁ። | | | | |
| 114 | ማስተናገድ፥ ማጽዳትና የመሳሰሉት የቤተ ክርስቲያን ዕርዳታ ስራዎች ይስማሙኛል። | | | | |
| 115 | አዲስ ኪዳንን ለሌሎች ደኅና አድርጌ አብራራለሁ። | | | | |
| 116 | ለሕይወቴ ትክክለኛ የሚመስሉ ብቻ ሳይሆን የሆኑም ውሳኔዎችን እወስናለሁ። | | | | |
| 117 | በልሳን በምጸልይበት ወቅት የመንፈስ ቅዱስ ኀልውናና ክብር ይሰማኛል። | | | | |
| 118 | ጸልዩ የተፈጥሮ ሕግ የተፋለሰበት ጊዜ ኖሮ ያውቃል። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 119 | በቤተ ክርስቲያን ለሕሙማን የሚጸለይበት የተለየ ጊዜ ሲኖር እንድመራ ወይም እንድሳተፍ እጠየቃለሁ። | | | | |
| 120 | በልሣን የሚናገሩ አማኞች እንዲተረጉሙ እንዲጸልዩ እነግራቸዋለሁ። | | | | |
| 121 | ለአገልግሎት ተግባራዊ ግቦችን ከሌሎች ጋር የማቀድ ችሎታ አለኝ። | | | | |
| 122 | በሌላ ቦታ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር የሚያስችለኝን ቋንቋ ደኅና አድርጌ የመማር ችሎታ አለኝ። | | | | |
| 123 | ከክርስቶስ ትምህርቶች ጋር የማይሄዱና ሐሰት የሆኑትን መለየት እችላለሁ። | | | | |
| 124 | ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ሳስረዳ የማያምኑ ሰዎች ይገባቸዋል። | | | | |
| 125 | ፊት ለፊት ተገናኝቶ በመነጋገር የሳተውን የመመለስና ዝም ብሎ የተቀመጠውን ደግሞ የማንቀሳቀስ መሣሪያ ሆኜ አውቃለሁ። | | | | |
| 126 | ሁኔታዎች ቢከፉ እንኳ እግዚአብሔር ግን ተስፋውን እንደሚጠብቅ አምናለሁ። | | | | |
| 127 | ለእግዚአብሔር ሥራ የሚውል ብዙ ገንዘብ ማግኘት እችላለሁ። | | | | |
| 128 | ለተቸገሩ ምግብና መጠለያን አበርክቶ መስጠት እርካታን ይሰጠኛል። | | | | |
| 129 | ለራሴ ሕይወት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን ማግኘት እችላለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 130 | ቤተ ክርስቲያኔን የማገለግልበት ብቃትና ዕውቀት ስላለኝ ሌሎች ይከተሉኛል። | | | | |
| 131 | ሌሎች ሰዎች ሊደርስባቸው ከሚችል ቅጣትና መቀጮ የማዳን ችሎታ አለኝ። | | | | |
| 132 | የእግዚአብሔርን እውነት ግሩምና ድንቅ በሆነ መንገድ አውጃለሁ። | | | | |
| 133 | የክርስቶስን ተከታዮች ከመጽሐፍ ቅዱስ በተውጣጡ ክፍሎች በመምራት መመገብ እችላለሁ። | | | | |
| 134 | በክፍል ውስጥ የአስተማሪ ረዳት መሆን ወይም በመሰል ተግባር መሰማራት ችሎታዩ ነው። | | | | |
| 135 | የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ለሌሎች ስናገር የዕውቀት፣ የአቀባበል፣ የአኳኋን፣ የአኗኗርና የጠባይ ለውጦች ይፈጠራሉ። | | | | |
| 136 | በክርስቲያናዊ አገልግሎት የምመርጣቸው ምርጫዎች ሁሉ ፍሬያማ ናቸው። | | | | |
| 137 | በልሳን ስጸልይ ራሴን እንዴት እንደማንጽ ይገባኛል። | | | | |
| 138 | በጣም ከባድ ነገሮችን ሊያደርጉ ከሚሞክሩ ሰዎች ጋር መተባበር ያስደስተኛል። | | | | |
| 139 | ለሕመማን ከሚጸልዩ አገልጋዮች ጋር መተባበር ልማዱም ደስታዩም ነው። | | | | |
| 140 | በልሳን የሚነገር መልዕክት ሲኖር የትርጉም መልእክት ለመቀበል በጣም ዝግጁ ሆኜ እጠባበቃለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 141 | ሥነ-ሥርዓትን ተከትሎ ትልቅ ለውጥን በማምጣት ረገድ ከቤተ ክርስቲያን አባላት ሰፊ ተቀባይነት አገኛለሁ። | | | | |
| 142 | አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሌላ ቋንቋና ባህል ባላቸው ዘንድ እንዲከፈቱ መርዳት እችላለሁ። | | | | |
| 143 | አስመሳይ ሰዎችን ሌሎች ሰዎች ስህተተኛነታቸውን ከመረዳታቸው በፊት አውቃለሁ። | | | | |
| 144 | በማያምኑ ጓደኞች መካከል በመንፈሣዊ ጥንካሬ በመቆየትና አጋጣሚዎችን ሁሉ በመጠቀም አንዳንዶቹን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ይሆንልኛል። | | | | |
| 145 | የተጨነቀን፥ ወንጀለኛንና ሱሰኛን ደህና አድርጌ ማማከርና መርዳት እችላለሁ። | | | | |
| 146 | እግዚአብሔር አንድን ዓላማ እንደሚ ፈጽም ከእርሱ ልዩ የሆነ እርግጠኛነት አለኝ። | | | | |
| 147 | ለእግዚአብሔር ሥራ በልግስና መስጠት እንዲቻለኝ ገንዘቤን በሚገባ መያዝ እችላለሁ። | | | | |
| 148 | በቤቱ ለሚመጡ እንግዶች የሚገባቸውን ግሩም አቀባበል አደርጋለሁ። | | | | |
| 149 | አእምሮንና ልብን የሚነኩ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን የማወቅና የማየት ችሎታ አለኝ። | | | | |
| 150 | ከኔ ጋራ እንደሚሰሩ ሰዎች ብስለት መጠን የአመራር ዘይቤዬን መለዋወጥ እችላለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ. | ጠቋሚ መጠይቅ | (3) በጣም | (2) በመጠኑ | (1) ጥቂት | (0) ምንም |
|---|---|---|---|---|---|
| 151 | ብቸኞች ከሆኑና ጠያቂ ከሌላቸው ጋር ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ መነጋገር እችላለሁ። | | | | |
| 152 | በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አማካይነት የእግዚአብሔርን የወደፊት ሥራዎች ጠቅለል ባለ ሁኔታ መናገር እችላለሁ። | | | | |
| 153 | ከክርስቲያን ኅብረተሰብ አካባቢ የኮበለሉ ሰዎችን የመመለስ ችሎታ አለኝ። | | | | |
| 154 | በጸሎትና በቃሉ የሚተጉ መሪ አገልጋዮችን በሌሎቹ አገልግሎቶች ጊዜአቸው እንዳይወሰድ መርዳት እችላለሁ። | | | | |
| 155 | አስቸጋሪ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ሌሎች ሰዎች ያለችግር መረዳት እንዲችሉ ማድረግ እችላለሁ። | | | | |
| 156 | ለቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ሥፍራ መመረጤ ተገቢ ምርጫ መሆኑ ብዙ ጊዜ ይረጋገጥልኛል። | | | | |
| 157 | በልሳን የምናገረው በራሴም ይሁን በሌላ እንዲተረጎም እጸልያለሁ። | | | | |
| 158 | ለአዕምሮ የሚከብዱ አስቸጋሪ ነገሮች አማኞችን ሲገጥሙ ጣልቃ ገብቼ ስለ ጌታ ቻይነት እንድናገርና እንድጸልይ እጋበዛለሁ። | | | | |
| 159 | መድኃኒት ላልተገኘላቸውም በሽታዎች የመጸለይ ድፍረት አለኝ። | | | | |
| 160 | ብዙ ጊዜ በልሳን የተነገሩ መልዕክቶችን በሚታወቅ የጉባዔ ቋንቋ ተርጉሜ ምዕመናን ተባርከዋል። | | | | |

# ክፍል ሦስት

1. በራሴ ምኞት የማገኘው ቢሆን እንዲኖሩኝ የምመኛቸው ሦስት ስጦታዎች?

ሀ. ለ. ሐ.

2. ብዙ ነጥቦች ያሏቸው ሦስት ስጦታዎች?

ሀ. ለ. ሐ.

3. የመጨረሻዎቹ ጥቂት ነጥቦች ያሏቸው ሦስት ስጦታዎች?

ሀ. ለ. ሐ.

4. ከስጦታዎቼ መካከል ጠቀም ያሉ ነጥቦች ኖሯቸውም ሌሎች በሳል አማኞችም እንዳሉኝ የመሰከሩልኝ ስጦታዎች?

ሀ. ለ. ሐ.

5. ከመጠይቁ በፊት እንዳሉኝ አስባቸው የነበሩ ስጦታዎች?

ሀ. ለ. ሐ.

6. ከራሴም ከሌሎች ሰዎችም ከመጠይቁም ነጥቦች ጋር የተስማሙ ስጦታዎች?

ሀ. ለ. ሐ.